

# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ




## ሁለተኛ ክፍል

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

 

# ሒሳብ

# የተማሪዉ መጽሐፍ

# 2ኛ ክፍል


**አዘጋጆች፡**

መ/ር ፊሊጶስ እሥራኤል

መ/ር ቤታ በቀለ

መ/ር ከተማ ካና

**አርታኢ፡**

መ/ር ኮሚንስት ወንጂ

**ጥራት ገምጋሚ፡**

መ/ር ሹርማሌ ገዴኖ

**ማረጋገጫ ሰጪዎች**

መ/ር ዘለቀ ማርቆስ

መ/ር ተመስገን ተስፋዬ

**ለመጽሐፉ መደረግ ያለባቸዉ ጥንቃቄዎች**

- መጽሐፉን በፕላስቲክ፣ አሮጌ ጋዘጣ እና መሰል ነገሮች ሸፍናችሁ ያዙ።
- ሁልጊዜ ንጹሕ እና ደረቅ በሆነ ቦታ አስቀምጡ።
- መጽሐፉን ስትጠቀሙ እጃችሁ ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ።
- በመጽሐፉ ሽፋን ሆነ በዉስጡ አትጻፉ።
- የመጽሐፉን ገጾች አትቅደዱ አትቁረጡ።
- መጽሐፉ ሲቀደድ ወይም ሲገነጠል በሙጫ እና መሰል በሆኑ ነገሮች እድሳት አድርጉ።
- በቦርሳችሁ ስታስቀምጡ በጥንቃቄ አስቀምጡ።
- ለሌላ ሰዉ ስታዉሱ በጥንቃቄ አዉሱ።

# ማውጫ


ምዕራፍ 1 ........ 1

እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ........ 1

1.1. የ 100 ብዜቶችን መቁጠር ........ 2

1.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ........ 7

1.3. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ........ 14

1.4. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ማወዳደር ........ 20

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ........ 26

ምዕራፍ 2 ........ 31

ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ........ 31

2.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ........ 32

2.1.1 እስከ 1,000 ያሉ የ10 እና የ 100 ብዜቶችን መደመር ........ 32

2.1.2. እስከ 1,000 ያሉ ያለአለኝታ የሚደመሩ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ........ 34

እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ መደመር ........ 36

2.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ........ 38

2.2.1. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን መቀነስ ........ 39

2.2.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ ብድር መቀነስ ........ 40

2.2.3. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በብድር መቀነስ ........ 42

2.3. ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 45

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች ........ 49

ምዕራፍ 3 ........ 52

እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማባዛት ........ 52

3.1. እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 ማባዛት ........ 53

3.2. እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ 10 ማባዛት ........ 56

3.3. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 1 ማባዛት ........ 61

3.4. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ማባዛት ........ 65

3.4.1 በሦስት ማባዛት ........ 66

3.4.2. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 4 እና በ 5 ማባዛት ........ 70

3.4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 6 እና በ 7 ማባዛት ........ 73

3.4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 8 እና በ 9 ማባዛት ........ 79
3.5. የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 82
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ........ 85
ምዕራፍ 4 ........ 89
ግማሽ እና ሩብ ........ 89
4.1. ግማሽ ........ 90
4.2. ሩብ ........ 94
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ........ 98
ምዕራፍ 5 ........ 101
ሥርዓተ- ጥለት (ፓቴርን) ........ 101
5.1. የድግግሞሽ ሥርዓተ-ጥለት ምድብ ........ 102
5.2. የጎደሉ የሥርዓተ-ጥለት አባላት ........ 105
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ........ 109
ምዕራፍ 6 ........ 112
የርዝመት ፣ የክብደት እና የይዘት መለኪያዎች ........ 112
6.1. ርዝመትን በባህላዊ፣በሜትር እና በሳንቲ ሜትር ምድቦች መለካት ........ 113
6.2. ተመሳሳይነት ያላቸዉን የርዝመት ምድብ መለኪያዎችን መደመር እና መቀነስ ........ 117
6.3. ክብደትን በግራም እና በኪሎግራም ምድቦች መለካት ........ 121
6.4. ተመሳሳይነት ያላቸዉን የክብደት ምድብ መለኪያዎችን መደመርና መቀነስ ........ 124
6.5. ይዘትን በሊትርና ሚሊ ሊትር ምድቦች መለካት ........ 128
6.6. ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት ምድብ ያላቸዉ የይዘት መጠን መለኪያዎችን መደመር እና መቀነስ 131
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ........ 134
ምዕራፍ 7 ........ 139
የመረጃ አያያዝ ........ 139
7.1. መረጃ መሰብሰብ ........ 140
7.2. ከሥዕላዊ ግራፍ መረጃዎችን በየአይነታቸዉ ማደራጀት ........ 146
7.3. ዕቃዎችን በመጠቀም መረጃ ማደራጀት እና መተንተን ........ 152
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች ........ 157
ምዕራፍ 8 ........ 159
የጂኦሜትሪ ቅርጾች ........ 159
8.1 ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾችን በማየት መመደብ ........ 160

8.2 ቅርጾችን በጎናቸዉ እና በነቁጣቸዉ መግለጽ ..... 163
8.3. ተመሳሳይ ምሥሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር ..... 168
8.4 ጠጣር ምስሎችን መለየት ..... 171
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ..... 174
ምዕራፍ 9 ..... 175
የኢትዮጵያ ገንዘብ ..... 176
9.1. የኢትዮጵያን ምንዛሪ በመጠቀም ገንዘብን መደመር እና መቀነስ ..... 177
9.2 በጨዋታ መልክ መገበያየት ..... 182
9.3 የቃላት ፕሮብሌሞች ..... 185
የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ ..... 188
ምዕራፍ 10 ..... 190
የኢትዮጵያ ጊዜ ..... 190
10.1 በድጅታል እና በአናሎግ ሰዓት ጊዜን በአንድ ሰዓት፣ በግማሽ ሰዓት እና በሩብ ሰዓት መቁጠር 191
10.2. ሰዓት እና ደቂቃ ..... 197
10.3. የቃላት ፕሮብሌሞች ..... 200

# ምዕራፍ 1

## እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ የ 100 ብዜቶች፤ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች፤ እስከ 1,000 ያሉ የሙሉ ቁጥር ቤት እና እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር ይሆናል፡፡ ስለዚህ በአንደኛ ክፍል እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን የተማራችሁትን ሀሳብ እስከ 1,000 ድረስ ባሉ ቁጥሮች እንዴት ማወቅ እንዳለባችሁ ምዕራፉ በስፋት ስለሚያብራራ እያንዳንዱን ምሳሌ እና መልመጃዎችን በመስራት የተሻለ ዕዉቀት ማግኘት ይቻላል፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የዕቃዎችን ብዛት በአቀማመጣቸዉ ቆጥራችሁ ትረዳላችሁ፡፡
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትለያላችሁ፤ በቅደም ተከተላቸውም ታስቀምጣላችሁ፡፡

## 1.1. የ 100 ብዜቶችን መቁጠር

መግቢያ፡

ተማሪዎች የ 100 ብዜቶችን እንዲለዩ፤ በቅደም ተከተላቸዉ እንዲያስቀምጡ እና የተለያዩ ዕቃዎችን መቶ በመቶ እንዲቆጥሩ ማስቻል፡፡ ይህም ቁጥሮችን እስከ 1,000 በሚማሩበት ጊዜ ይረዳቸዋል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ የመቶ ብዜቶችን ይለያሁ፡፡
- የ 100 ብዜቶችን ይቆጥራሉ፡፡
- የ 100 ብዜቶችን ይጽፋሉ፡፡

## ተግባር 1.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩባቸዉ፡፡

   ሀ. እስከ 100 ያሉትን የ 10 ብዜቶች ጻፉ፡፡

   ለ. ከ 50 የሚያንሱ የ 10 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?

   ሐ. ስንት አሥሮች መቶ ይሆናሉ?

   መ. መቶ ስንት ዜሮዎች አሉት?

   ሠ. መቶ ላይ መቶ ስንደምር ስንት ይሆናል?

ማስታወሻ፡- ቁጥሮችን ስንቆጥር ቀጣዩን ቁጥር ለማግኘት በቁጥሮች ላይ አንድን እንደምራለን፡፡ የ 10 ብዜቶችን በቅደም ተከተል ለመጻፍ ከ 10 በመጀመር አሥር አሥር እንደምራለን፡፡ የ 100 ብዜቶችን በቅደም ተከተል ለመጻፍ ከ 100 በመጀመር መቶ መቶ እንደምራለን፡፡

ምሳሌ-1 አንድ ቅርጫት 100 ሎሚዎችን የሚይዝ ከሆነ ቀጥለዉ የቀረቡትን የቅርጫት ሥዕሎች በመቁጠር ምን

ያህል ሎሚዎች እንዳሉ ብዛታቸዉን በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡




መፍትሔ፡ ሀ. 200 ለ. 300 ሐ. 400 መ. 500

ምሳሌ- 2 ከዚህ በታች ያሉትን የካሬዎችን ብዛት የሚያሳዩ ሠንጠረዦችን በመጠቀም ትክክለኛ የካሬ ብዛታቸዉን በመቁጠር ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡



**መፍትሔ:** ሀ. 100 ለ. 300

ምሳሌ 3 አንድ እሥር 100 እንጨቶችን ይይዛል፡፡ የእሥሮችን ብዛት በመቁጠር በጠቅላላዉ ስንት እንጨቶች እንዳሉ ትክክለኛ መልሳቸዉን በባዶ ቦታ ላይ ሙሉ፡፡




**መፍትሔ:** ሀ. 300 ለ. 400

ምሳሌ-4 የጎደሉ የመቶ ብዜቶችን በቁጥር መስመር ላይ ሙሉ፡፡




**መፍትሔ:** ሀ. 300፣ 400፣ 500፣ 700፣ 800፣ 900

ምሳሌ 5. የሚከተሉትን የመቶ ብዜቶች ስያሜ በቃላችሁ ጥሩ፡፡

ሀ.800 ለ.500 ሐ.300 መ. 900

## መልመጃ 1.1

1. ከዚህ በታች ያለዉን ሠንጠረዥ በመጠቀም ትክክለኛ የካሬዎችን ብዛት በባዶ ቦታ ሙሉ፡፡



______ × ______ = _______________

2. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በቁጥር መስመር ላይ ሙሉ፡፡

ሀ. 


3. ከዚህ በታች ያሉ የመቶ ብዜቶችን ስያሜ በፊደል ጻፉ፡፡

ሀ. 100 ____________________________________

ለ. 200 ____________________________________

ሐ. 500 ____________________________________

መ. 900 ____________________________________

4. የሚከተሉትን በማባዛት ትክክለኛ መልሳቸዉን በባዶ ቦታዎች ላይ ሙሉ፡፡

ሀ. 1 × 100 = ______

ለ. 3 × 100 = ______

ሐ. 8 × 100 = ______

መ. 9 × 100 = ______

ሠ. 10 × 100 = ______

5. ከዚህ በታች ላሉ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሳቸዉን በጎደሉ በታዎች ሙሉ፡፡

ሀ.______ + 100 = 700　　ለ.______ + 200 = 500

ሐ. 400 + ______= 900　　መ.600 + ______= 800

## 1.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች

**መግቢያ፡** በዚህ ርዕስ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለማወቅ በመጀመሪያ እስከ 1,000 ያሉት የ 10 እና የ 100 ብዜቶች በክለሳ መልክ የቀረቡ ሲሆን በመቀጠል በ 10 ብዜቶች መካከል ያሉ ቁጥሮች እንዴት እንደሚጻፉ በተግባር እና በምሳሌ የቀረቡትን በመረዳት መልመጃዎችን መስራት ይቻላል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ፡፡
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትጽፋላችሁ፡፡

## ተግባር 1. 2

1. ከሚከተሉት የመቶ ብዜት ያልሆኑት የትኞች ናቸዉ?

   ሀ. 100    ለ.830    ሐ.450    መ.800    ሠ. 900

2. በ 100 እና በ 800 መካከል ያሉ የ 100 ብዜቶችን ጻፉ፡፡
3. ከ 900 እስከ 1,000 ያሉ የ 10 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?
4. ከ 100 እስከ 110 ያሉትን ቁጥሮች ፃፉ፡፡

   ምሳሌ 101 102 103 104 105 --- 110

**ማስታወሻ፡-** ከ101 — 199 ለመቁጠር ከ 1-99 ያሉ ቁጥሮችን ከመጥራታችን በፊት አንድ መቶ የሚለዉን ቃል አስቀድመን እንጠራለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ከ 1 — 99 ባሉ ቁጥሮች መጀመሪያ ላይ ሁለት መቶ፤ ሦስት መቶ፤ አራት መቶ፤ አምስት መቶ፤ ስድስት መቶ፤ ሰባት መቶ፤ ስምንት መቶ እና ዘጠኝ መቶን አስቀድመን በመጥራት እስከ 999 መቁጠር መለማመድ ይቻላል፡፡

ምሳሌ.1

| | | | |
|---|---|---|---|
| አንድ | 1 | አንድ መቶ አንድ | 101 |
| ሃያ አራት | 24 | አንድ መቶ ሃያ አራት | 124 |
| ሰላሳ አምስት | 35 | አንድ መቶ ሰላሳ አምስት | 135 |
| ሰማኒያ ሰባት | 87 | ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት | 287 |
| ዘጠና ዘጠኝ | 99 | ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ | 999 |

ምሳሌ 2. የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንብቡ፡፡

ሀ.



3 x 100 + 1x50 = 350

ለ.



2x200 + 1x100 + 1x1 = 501

ሐ.



5 x 100 + 2 x 10 + 1 x 5 = 525

ምሳሌ 3 የጎደለዉን በመሙላት የቁጥሮችን ስያሜ ጻፉ፡፡

ሀ. 100 + 1 =_____

ለ. 200 + 1 = _____

ሐ. 300 + 1 = _____

መ. 800 + 1 = _____

ሠ. 900 + 1 = ____

መፍትሔ፡ ሀ. 101 ለ. 201 ሐ.301

መ. 801 ሠ. 901

ምሳሌ 4. ከ 100 እስከ 200 ያሉ የአሥር ብዜቶችን አንብቧቸዉ፡፡

መፍትሔ፡ 100, 110, 120, 130, 140, 150, 160, 170, 180,190, 200

ምሳሌ 5፡ ሀ. በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል በመጻፍ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 501 | | | | 505 | | | | | 510 |
| | 512 | | | | | 517 | | 519 | |
| | | 523 | | | | | 528 | | |
| | 532 | | 534 | | | 537 | | | |
| | | | | 545 | 546 | | | | |
| 551 | | | | 555 | 556 | | | | 560 |
| | | | 564 | | | 567 | | 569 | |
| | | 573 | | | | | 578 | | |
| | 582 | | | | | 587 | | 589 | |
| 591 | | | | 595 | | | | | 600 |

ለ. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከ 555 በመጀመር ከቀኝ ወደግራ፤ ከግራ ወደቀኝ፤ ከላይ ወደታች እና ከታች ወደላይ ቁጠሩ፡

**መፍትሔ ሀ.**

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 501 | 502 | 503 | 504 | 505 | 506 | 507 | 508 | 509 | 510 |
| 511 | 512 | 513 | 514 | 515 | 516 | 517 | 518 | 519 | 520 |
| 521 | 522 | 523 | 524 | 525 | 526 | 527 | 528 | 529 | 530 |
| 531 | 532 | 533 | 534 | 535 | 536 | 537 | 538 | 539 | 540 |
| 541 | 542 | 543 | 544 | 545 | 546 | 547 | 548 | 549 | 550 |
| 551 | 552 | 553 | 554 | 555 | 556 | 557 | 558 | 559 | 560 |
| 561 | 562 | 563 | 564 | 565 | 566 | 567 | 568 | 569 | 570 |
| 571 | 572 | 573 | 574 | 575 | 576 | 577 | 578 | 579 | 580 |
| 581 | 582 | 583 | 584 | 585 | 586 | 587 | 588 | 589 | 590 |
| 591 | 592 | 593 | 594 | 595 | 596 | 597 | 598 | 599 | 600 |

## መፍትሔ ለ፡ ክፍል ዉስጥ ተማሪዎችን ማስቆጠር

### መልመጃ 1.2

1. የካሬዎችን ብዛት በመቁጠር በጎደሉ ቦታዎች ሙሉ።

ሀ



_____ × _____ + ____×____ + __×__ = _____

ለ



____ × ____ + ____×____+ ____×____ = ______

2. ከዚህ በታች ያሉ ጥያቄዎችን ደምሩ።

ሀ. 100 + 2 = _______ ለ. 100 + 3 = _______

ሐ. 900 + 4 = _______ መ. 100 + 5 = _______

ሠ. 800 + 7 = _______

3. ከ 700 እስከ 800 ያሉ የአሥር ብዜቶችን ጻፉ።

______ ______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ _____ _____

4. ከዚህ በታች ያሉ ቁጥሮችን ወደፊትና ወደኋላ ቁጠሩ፡፡

900, 901, 902, 903, 904, 905, 906, 907, 908, 909, 910

5. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ጻፉ፡፡

ሀ. 304 ______________________________________

ለ. 502 ______________________________________

ሐ. 907 ______________________________________

መ. 910 _________________________________

6. የሚከተሉትን በአሃዝ ጻፉ፡፡

ሀ. ሁለት መቶ ሁለት ____________

ለ. ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ____________

ሐ. አምስት መቶ አምስት ____________

መ. ስድስት መቶ ሃምሳ ሰባት____________

## 1.3. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት

**መግቢያ፡**

በዚህ ንዑስ ርዕስ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋ እንዴት እንደሚቀመጥ እና እንደሚጠራ የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም በምሳሌዎች የተሠራ ስለሆነ ይህንን በመረዳት መልመጃዎችን በቀላሉ መሥራት ይቻላል።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን የቁጥር ቤት ትለያላችሁ።
- የቁጥር ቤቶችን ዋጋ ትገነዘባላችሁ።

**ተግባር 1.3**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩ።

ሀ. የምታዉቁት የቁጥር ቤቶች እነማን ናቸዉ?

ለ. የቁጥር ቤት እያደገ ወይም እየጨመረ የሚሄደዉ ከቀኝ ወደ ግራ ነዉ? ወይስ ከግራ ወደ ቀኝ ነዉ?

ሐ. ባለ አንድ ሆሄ የቁጥር ቤት ስንት ነዉ?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. በ 8 ዉስጥ ስንት አንዶች አሉ?

ለ. በ 30 ዉስጥ ስንት አሥሮች አሉ?

ሐ. በ 500 ዉስጥ ስንት መቶዎች አሉ?

መ. በ 538 ዉስጥ ስንት መቶዎች፤ ስንት አሥሮች እና ስንት አንዶች አሉ?

ማስታወሻ፡

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች የአንድ ቤት ናቸዉ፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች በስተቀኝ ያለዉ የአንድ ቤት ሲሆን በስተግራ ያለዉ የአሥር ቤት ነዉ፡፡
- ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮች በስተቀኝ ያለዉ የአንድ ቤት ፤ መሃል ያለዉ የአሥር ቤት፤ በስተግራ ያለዉ የመቶ ቤት ናቸዉ፡፡

ምሳሌ 1. ከዚህ በታች ባለዉ ሠንጠረዥ በመቶ ቤት 4 መቶዎች፤ በአሥር ቤት 6 አሥሮች እና በአንድ ቤት 5 አንዶች ይገኛሉ፡፡ ይህም ሲጻፍ 465 ተብሎ ይጻፋል፡፡



| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 4 | 6 | 5 |

ምሳሌ 2 . ቁጥሮች በቁጥር ቤት በአባካስ ሲቀመጡ፡-




ሀ. በሚታዩት አባካስ ዉስጥ 4 አንዶች፣ 4 አሥሮች እና 3 መቶዎች አሉ፡፡ ይህም 344 ተብሎ ይጻፍል፡፡ ሲነበብ ሦስት መቶ አርባ አራት ይባላል፡፡

ለ. 897ን በቁጥር ቤት ስናስቀምጥ፡-

| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 8 | 9 | 7 |

በፊደል ሲጻፍ <u>ስምንት መቶ ዘጠና ሰባት</u>

ሐ. በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ያለዉን የቤቶች ዋጋ በመቁጠር ከታች ባለዉ ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡




| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| | | |

**መፍትሔ**

| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 7 | 6 | 2 |

## መልመጃ 1.3.

1. የሚከተሉትን ከአባካስ በማየት ብዛታቸዉን በየቁጥር ቤት ሙሉ።

ሀ. 

| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| | | |

= ____________

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በየቤታቸዉ እና በፊደል ጻፉ።

| ሙሉ ቁጥር | የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት | በፊደል ሲጻፍ |
|---|---|---|---|---|
| 984 | 9 | 8 | 4 | ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አራት |
| 536 | | | | |
| 421 | | | | |
| 245 | | | | |
| 867 | | | | |

3. እያንዳንዱን ሆሄ በቁጥር ቤታቸዉ ጻፉ።

ሀ. 435 ___ የመቶ ቤት ___የአሥር ቤት __ የአንድ ቤት

ለ. 960 ___ የመቶ ቤት ___ የአሥር ቤት __የአንድ ቤት

ሐ. 823 ___ የመቶ ቤት ___ የአሥር ቤት___ የአንድ ቤት

መ. 218 _____ የመቶ ቤት___ የአሥር ቤት___ የአንድ ቤት

ሠ. 609 ____ የመቶ ቤት ____የአሥር ቤት ____ የአንድ ቤት

4. የሚከተሉትን አባካሶች በመጠቀም የተሰጡትን ቁጥሮች ብዛት በየቤታቸዉ በሥዕል አሳዩ።



ሀ. 671 ለ. 902 ሐ.465

5. በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ያሉ የቤቶችን ብዛት በመቁጠር ከታች ባለዉ በሆሄ ቤት ዋጋ ሙሉ።




| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| | | |

## 1.4. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ማወዳደር

**መግቢያ፡** በዚህ ንዑስ ርዕስ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በቅደም ተከተል እንዴት እንደሚቀመጡ እና በይበልጣል፣ያንሳል እና እኩል ይሆናል ምልክቶችን በመጠቀም እንዴት ማወዳደር እንደሚቻል በምሳሌዎች ተገልጿል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ፡፡
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በይበልጣል፤ ያንሳል እና እኩል ይሆናል ምልክቶች ታወዳድራላችሁ፡፡

## ተግባር 1.4

ሀ. የ 100 ተከታይ ቁጥር ስንት ነዉ?

ለ. የ 100 ቀዳማይ ቁጥር ስንት ነዉ?

ሐ. ከ 200 በአንድ የሚበልጥ ቁጥር ማን ነዉ? በአንድ የሚያንስ ቁጥር ማን ነዉ?

መ. በክፍላችሁ ያሉ የሴት እና የወንድ ተማሪዎች ብዛት እኩል ነዉ? የትኛዉ ይበልጣል? የትኛዉ ያንሳል? እኩል ለማድረግ ስንት ወንድ ወይም ስንት ሴት ተማሪዎች ያስፈልጋሉ?

ማስታወሻ፡- በቁጥር መስመር ላይ በስተቀኝ ያለዉን ቁጥር ለማግኘት አንድ እንደምራልን፡፡ በስተ ግራ ያለዉን ቁጥር ለማግኘት አንድ እንቀንሳለን፡፡

| ምልክት | ስያሜ |
|---|---|
| > | ይበልጣል |
| < | ያንሳል |
| = | እኩል ይሆናል |

ባለሦስት ሆሄ ቁጥሮችን ስናወዳድር በመጀመሪያ የመቶ ቤቶችን እናወዳድራለን፡፡ የመቶ ቤት ትልቅ የሆነዉ የመቶ ቤት ትንሽ ከሆነዉ ይበልጣል፡፡ የመቶ ቤቶች እኩል ከሆኑ የአሥር ቤቶችን እናወዳድራለን፡፡ የአሥር ቤት ትልቅ የሆነዉ የአሥር ቤት ትንሽ ከሆነዉ ይበልጣል፡፡ የመቶ እና የአሥር ቤቶች እኩል ከሆኑ የአንድ ቤቶች እናወዳድራለን፡፡ የመቶ እና የአሥር ቤት እኩል ሆኖ የአንድ ቤት የሚበልጠዉ ይበልጣል፡፡ የሚያንሰዉ ያንሳል፡፡ የመቶ፤ የአሥር እና የአንድ ቤት እኩል ከሆኑ ቁጥሮቹ እኩል ይሆናሉ፡፡

ምሳሌ

1. ከዚህ በታች ያሉ 800 801 802 803 ቁጥሮችን ወደፊትና ወደኋላ ቁጠሩ፡፡
2. የሚከተሉትን እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. የ 801 ቀዳማይ 800 ነዉ፡፡ _________

ለ. የ 801 ተከታይ 802 ነዉ፡፡ _________

መፍትሔ፡ ሀ. እዉነት ለ. እዉነት

3. የ 205 ቀዳማይ ______ ሲሆን የ 205 ተከታይ _______ ነዉ፡፡

መፍትሔ፡- የ 205 ቀዳማይ ለማግኘት ከ 205 ላይ አንድ መቀነስ ነዉ፡፡

205 — 1 = 204

የ 205 ተከታይ ለማግኘት በ 205 ላይ 1 ን መደመር ነዉ፡፡

205 + 1 = 206

4. በቁጥር መስመር ላይ ያሉ ቁጥሮችን በመመልከት ከታች ባለዉ ክፍት ቦታ ላይ ለሚገኙ ቁጥሮች ቀዳማይና ተከታይ ፈልጉ፡፡




. ሀ. የ84 ቀዳማይ 83 ነዉ፡፡

ለ. የ84 ተከታይ 85 ነዉ፡፡

ሐ. የ 82 ቀዳማይ ______ነዉ፡፡

መ. የ 82 ተከታይ ______ ነዉ፡፡

መፍትሔ፡ ሐ. 81 መ. 83

5. የሚከተሉትን ይበልጣል( >)፤ ያንሳል( < )ወይም እኩል ይሆናል (= ) ምልክቶች አወዳድሩ፡፡

ሀ. 125 < 126 ለ.293___290 ሐ. 888___888

**መፍትሔ፡** ለ. 293 > 290 ሐ. 888 = 888

## መልመጃ 1-4

1. በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. | 600 | | 602 | | | | 606 |
| ለ. | 899 | | | | 903 | | 905 |

2. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቁጥሮች ተከታይና ቀዳማይ ጻፉ።

ሀ. 150 ቀዳማይ______ ተከታይ ______ነዉ።

ለ. 272 ቀዳማይ______ ተከታይ ______ነዉ።

ሐ. 809 ቀዳማይ______ ተከታይ ______ነዉ።

መ. 776 ቀዳማይ______ ተከታይ ______ነዉ።

3. ከዚህ በታች ያሉ እንጨቶች መቶ በመቶ የታሰሩ ናቸዉ። የእንጨቶችን ብዛት ይበልጣል(>)፤ ያንሳል(<) ወይም እኩል ይሆናል(=) ምልክቶች በመጠቀም አወዳድሩ።





4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይበልጣል(>)፤ ያንሳል(<) ወይም እኩል ይሆናል(=) ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. 860_____783 መ. 425_____425

ለ. 524_____630 ሠ. 824 _____700

ሐ. 220_____329 ረ. 407_____470

5. የሚከተሉትን በቁጥር መስመር በማየት ቀዳማይ እና ተከታዩን ጻፉ፡፡




ሀ. የ 63 ቀዳማይ ማን ነዉ? ___________

ለ. የ 63 ተከታይ ማን ነዉ? ___________

ሐ. የ 62 ቀዳማይ ማን ነዉ? ___________

መ. 62 ተከታይ ማን ነዉ? ___________

6. ከመምህራችሁ የመቶ ብዜት የያዙ ካርዶችን በመዉሰድ በቅደም ተከተል አስቀምጡአቸዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

- እስከ 1,000 ያሉ የ 100 ብዜቶች 100 ን ከ 1 እስከ 10 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ስናባዛ የምናገኘዉ ዉጤት ነዉ፡፡
- ቁጥሮችን ለማንበብ የቁጥር ቤት ዋጋ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
- የአንድ ቁጥር ቀዳማይ ማለት በቁጥር መሥመር ላይ ከተሰጠዉ ቁጥር በስተግራ ያለዉ ቁጥር ሲሆን ተከታይ ማለት ከተሰጠዉ ቁጥር በስተቀኝ ያለዉ ቁጥር ነዉ፡፡

**የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

   ሀ. በመቶ ዉስጥ አሥር አሥሮች አሉ፡፡

   ለ. የ 32 ቀዳማይ 33 ነዉ፡፡

   ሐ. የ 999 ተከታይ 1,000 ነዉ፡፡

   መ. 256 $\geq$ 258

   ሠ. አንድ ሺ ባለ ሦስት ሆሄ ነዉ፡፡

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡

   ሀ. 701 703 702 700

   ________ ________ ________ ________

ለ. 800 825 897 874

_______ _______ ________ ________

ሐ. 501 503 504 507

_______ _______ ________ ________

መ. 900 890 889 901

_______ _______ ________ ________

3. ከዚህ በታች ባሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙትን ሙሉ ቁጥሮች ጻፉ፡፡

ሀ. በ 589 እና 699 መካከል ያሉ ቁጥሮች

ለ. በ 100 እና በ 500 መካከል የሚገኙ የ 100 ብዜቶች

ሐ. በ 436 እና በ 470 መካከል ያሉ ቁጥሮች

4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይበልጣል (>)፤ ያንሳል (<)፤ እኩል (=) በማለት አወዳድሩ፡፡

ሀ. 250 _______ 249 ለ. 111 _______ 222

ሐ. 331 _______ 331 መ. 999 _______ 666

5.ካሬዎችን ብዛት በመፈለግ በጎደሉ ቦታዎች ሙሉ።



______ × ____ + ____ x ____ + ____ x ____ =

______

6.እያንዳንዱን ቁጥር በቁጥር ቤት ተንትኑ።

| ሙሉ ቁጥር | የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት | በፊደል ሲጻፍ |
|---|---|---|---|---|
| 479 | | | | |
| 832 | | | | |
| 100 | | | | |
| 504 | | | | |

7.የሚከተሉትን የብር ኖቶች መጠን ጻፉ።

ሀ.   

100 + 5 + 1 =______

ለ.   

2 × 200 + 1 × 10 = _______

ሐ. 

$2 \times 100 + 1 \times 50 =$ ______

8. በሚከተለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ ያሉ የቤቶችን ብዛት በመቁጠር ከታች ባለዉ በሆሄ ቤት ዋጋ ሙሉ።




| የመቶ ቤት | የአሥር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| | | |

9. ከዚህ በታች በቁጥር መስመር ላይ ያሉ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ።

ሀ. 


ለ. 

10. ከ 1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በደብተራችሁ ላይ በቅደም ተከተል በመጻፍ አንብቧቸዉ፡፡

# ምዕራፍ 2

## ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ

**መግቢያ፡** በዚህ ምዕራፍ ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ ይገኛል፡፡ በቅድሚያ የ 10 እና የ 100 ብዜቶች እንዴት እንደሚደመሩ እና እንደሚቀነሱ ተገልጿል፡፡ ከዚያም አለኝታዎች እንዴት እንደሚደመሩ እና ለመቀነስ እንዴት እንደምንበደር ማብራሪያና ምሳሌ ተሰጥቷል፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ፡፡
- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትቀንሳላችሁ፡፡

## 2.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

**መግቢያ፡** እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ለመደመር በዚህ ርዕስ የ 10 እና 100 ብዜቶች በቅድሚያ እንዴት እንደሚደመሩ ተገልጿል፡፡ ቀጥሎ አለኝታ የሌላቸዉ በየቤታቸዉ ተደምረዋል፡፡ ከዚያም ቁጥሮች በየቤታቸዉ አለኝታ ያላቸዉ እንዴት እንደሚደመሩ በምሳሌ ተብራርቷል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትደምራላችሁ፡፡

### 2.1.1 እስከ 1,000 ያሉ የ10 እና የ 100 ብዜቶችን መደመር

ተግባር 2.1.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየተወያያችሁ ደምሩ፡፡

ሀ. 20 + 10 = ______ ለ. 40 + 20 = ______

ሐ. 800 + 100 = ______ መ. 660 + 330 = _____

2. ወ/ሮ አይናቴ የሙዝ ነጋዴ ናት፡፡ ሙዝ የሚታስቀምጥባቸዉ ሁለት ቅርጫቶች አሏት፡፡አንደኛዉ ቅርጫት 20 ሙዞችን ይይዛል፡፡ ሁለተኛዉ ቅርጫት 60 ሙዞችን ይይዛል፡፡ ሁለቱ ቅርጫቶች አንድ ላይ ምን ያህል ሙዞችን መያዝ ይችላሉ?

3. አበበ 100 የባህር ዛፍ ችግኞች አሉት፡፡ አየለች ደግሞ 30 የባህር ዛፍ ችግኞች አሏት፡፡ አበበ እና አየለች በጋራ ስንት የባህር ዛፍ ችግኞች አሉአቸዉ?

**ማስታወሻ፡-** የ 10 ብዜቶችን ለመደመር አሥር በአሥር የሆኑ ዕቃዎች አንድ ላይ መደመር፡፡ የ 100 ብዜቶችን ለመደመር አንድ ላይ መደመር፡፡የ 100 እና የ 10 ብዜቶችን ለመደመር አሥር በአሥር የሆኑ ዕቃዎችን እና መቶ በመቶ የሆኑ ዕቃዎችን አንድ ላይ መደመር፡፡

ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ደምሩ፡፡

ሀ. 20 + 40 =60




ለ.100 + 200 =300



ሐ. 300 + 50 = 350




**መልመጃ 2.1.1**

1. የሚከተሉትን የ 10 እና የ100 ብዜቶች ደምሩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. 40 + 50 = ______ | ለ. 80 + 60 = ______ |
| ሐ. 200 + 70 = _____ | መ.300 + 100 =______ |
| ሠ. 50 + 100 = ______ | ረ.120 + 250 = ______ |
| ሰ. 70 + 550 = ______ | ሸ.630 + 60 = ______ |
| ቀ. 900 + 20 = ______ | በ. 450 + 350 =______ |

## 2.1.2. እስከ 1,000 ያሉ ያለአለኝታ የሚደመሩ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

**ተግባር 2.1.2**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. 322 + 1 =________ | ለ. 402 + 5 =______ |
| ሐ. 331 + 1 =_______ | መ. 900 + 8 =______ |

ማስታወሻ፡- ቁጥሮች ያለአለኝታ ሲደመሩ የአንድን ቤት ከአንድ ቤት ጋር፤ የአሥርን ቤት ከአሥር ቤት ጋር፤ የመቶን ቤት ከመቶ ቤት ጋር እንደምራለን፡፡

ምሳሌ 1 የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 380 + 10 =390　　　ለ.235 + 20 =255

ሐ. 323 + 22 =345　　　መ. 900 + 8 =908

ምሳሌ 2. የሚከተሉትን ባለ ሦስት ሆሄ ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 111 + 222 = 333　　　ለ. 421 + 124 = 545

ሐ. 950 + 40 = 990　　　መ.966 + 33= 999

## መልመጃ 2.1.2

1.የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 452 + 3 = ________　　　ለ. 888 + 1 = ________

ሐ.770 + 8 = ________　　　መ. 665 + 4 = ________

ሠ. 5 + 50 = ________　　　ረ. 55 + 23 = ______

ሰ. 65 + 20 = ________　　　ሸ. 45 + 14 = ______

2.የሚከተሉትን ባለሦስት ሆሄ ቁጥሮች ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ጋር ደምሩ፡፡

ሀ. 340 + 29 =______　　　ለ. 356 + 20 = _______

ሐ. 674 + 25 = ______　　　መ. 137 + 51 = _______

## እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአለኝታ መደመር

**ተግባር 2.1.3**

1. የሚከተሉትን ደምሩ፡፡

ሀ. 4 + 8 = _______  ለ. 15 + 9 = _______

ሐ. 18 + 22 = _______  መ. 57 + 37 = _______

**ማስታወሻ.** 173 + 244 በአለኝታ እንዴት እንደሚደመር ከዚህ በታች ተገልጿል፡፡




173 ን ከ 244 ጋር ለመደመር በአንድ ቤት 3 ን ከ 4 ጋር እንደምራለን፡፡ 7 ይሆናል፡፡ በአሥር ቤት 7 አሥሮች እና 4 አሥሮች 11 አሥሮች ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ አንድ አሥርን በአሥር ቤት በማስቀመጥ 10 አሥሮች አንድ መቶ ስለሚሆኑ ወደ መቶ ቤት በመዉሰድ ከ 3 መቶዎች ጋር ስንደምር 4 መቶዎች ይኖሩናል፡፡ በዚህ መሠረት የምናገኘዉ ዉጤት 417 ይሆናል፡፡

**ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ደምሩ።**

ሀ. 346 + 258 =___

መጀመሪያ የአንድ ቤት ይደመራል 6+8=14 , 14 = 10 + 4 , 4 በአንድ ቤት ይጻፋል። 10 ማለት 1 አሥር ስለሆነ ከአሥር ቤቶች ጋር ይደመራል። 1+4+5= 10 ይህም 10 አሥሮች አንድ መቶ ይሆናል። ስለዚህ 1 መቶ ከመቶ ቤቶች ጋር ይደመራል። 1+3+2= 6

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 1 | |
| | 3 | 4 | 6 |
| + | 2 | 5 | 8 |
| | 6 | 0 | 4 |

ስለዚህ መልሱ 604 ይሆናል።

መፍትሔ 346 + 258 =___ በመተንተን መደመር ይቻላል።

346 + 258 = 300 + 40 + 6 + 200 + 50 + 8

= 300 + 200 + 40 + 50 + 6 + 8

= 500 + 90 + 14

= 500 + 90 + 10 + 4

= 500 + 100 + 4

= 600 + 4

= 604

**መልመጃ 2.1.3**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በመተንተን ደምሩ።

ሀ. 508 + 423 = _______ ለ. 468 + 346 = ________

ሐ. 665 + 244 = ______    መ. 123 + 687 = ________

2. የሚከተሉትን ቁልቁል ደምሩ፡፡

| ሀ. 48 | ለ. 85 | ሐ. 642 | መ. 525 |
|---|---|---|---|
| + 24 | + 17 | + 60 | + 39 |
| _____ | ______ | ______ | ______ |

## 2.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

መግቢያ፡ በዚህ ርዕስ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ሲቀነሱ ያለ ብድር እንዴት እንደሚቀነሱ እና በብድር በየቤቱ እንዴት እንደሚቀነሱ በምሳሌ የቀረበ ስለሆነ ምሳሌዎችን በመረዳት መልመጃዎችን ሥሩ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትቀንሳላችሁ፡፡

### 2.2.1. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን መቀነስ

ተግባር 2.2.1

1. የሚከተሉትን ቀንሱ፡፡

ሀ. 90 — 70 = ____ ለ. 800 — 200 = ____

ሐ. 350 — 250 = ____ መ. 880 — 10 = ____

ማስታወሻ፡- እስከ 1,000 ያሉ የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን ስንቀንስ አሥር አሥር ወይም መቶ መቶ ከተሰጡ የ 10 ወይም የ 100 ብዜቶች ላይ እንቀንሳለን፡፡

ምሳሌ፡ የሚከተሉትን ቀንሱ፡፡

ሀ. 80 - 30 = 50




ለ. 500 — 100 = 400



**መልመጃ 2.2.1**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 100 — 10 = _____ ለ. 150 — 20 = _____

ሐ. 600 — 50 = _____ መ. 700 — 300 = _____

ሠ. 980 — 300 = _____ ረ. 860 — 320 = _____

## 2.2.2. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያለ ብድር መቀነስ

**ተግባር 2.2.2**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 199 — 1 = _____ ለ. 152 — 2 = _____

ሐ. 627 — 5 = _____ መ. 704 — 3 = _____

ሠ. 987 — 345 = _____ ረ. 86 — 32 = _____

ማስታወሻ፡ እስከ 1,000 ያሉ ቁጥሮችን ያለ ብድር ስንቀንስ ከአንድ ቤት የአንድን ቤት፤ ከአሥር ቤት የአሥርን ቤት እና ከመቶ ቤት የመቶ ቤትን እንቀንሳለን፡፡

ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 236 — 1 = ____ ለ. 568 — 2 = ____

ሐ. 989 — 5 = ____

መፍትሔ፡- ሀ) 236 — 1 = 235

ለ) 568 — 2 = 566

ሐ) 989 — 5 = 984

ምሳሌ 2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 895 — 23 = ____ ለ. 876 — 24 = ____

ሐ. 997 — 354 = ____

መፍትሔ፡- ሀ) 895 — 23 = 872

ለ) 876 — 24 = 852

ሐ) 997 — 354 = 643

ምሳሌ 3 የሚከተሉትን በመተንተን ቀንሱ

357 — 124 = 300 + 50 + 7 — 100 — 20 — 4

= 300 — 100 + 50 — 20 + 7 — 4

= 200 + 30 + 3

= 233

መልመጃ 2.2.2

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደጎን ቀንሱ፡፡

ሀ. 434 — 24 = ____ ለ. 662 — 11 = ____

ሐ. 956 — 11 = ____ መ. 690 — 40 = ____

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ቀንሱ፡፡

ሀ. 567 — 453 = ____ ለ. 489 — 376 = ____

ሐ. 815 — 204 = ____ መ. 687 — 577 = ____

ሠ. 785 — 144 = ____

### 2.2.3. እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በብድር መቀነስ

ተግባር 2.2.3

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

ሀ. 56 — 47= ____ ለ. 64 — 29 = ____

ሐ. 100 — 1 = ____ መ. 801 — 729 = ____

ማስታወሻ፡- ሙሉ ቁጥሮችን ስንቀንስ በየቤታቸዉ በተመሳሳይ ቁጥር ቤት ያሉ ሆሄያትን መቀነስ፡፡ ለመቀነስ በመጀመሪያዉ ቤት ያለዉ ቁጥር ከሁለተኛዉ ቤት የሚያንስ ከሆነ ቀጥሎ ካለዉ ቤት በመበደር ከዚህ በታች ባለዉ ምሳሌ መሠረት እንቀንሳለን፡፡



ምሳሌ፡ 33 — 26 = ____

33 3 አሥሮች እና 3 አንዶች አሉት፡፡ 26 2 አሥሮች እና 6 አንዶች አሉት፡፡ 6 አንዶችን ከ 3 አንድ መቀነስ ስለማይቻል ከ 3 አሥሮች አንዱን አሥር በመበደር አሥር አንድ ሆኖ ከ 3 አንድ ጋር 13 አንድ ሲቀነስ 6 አንድ 7 አንድ ይቀራል፡፡ ስለዚህ 33 — 26 = 7

**ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ቀንሱ፡፡**

ሀ. 287-126 = 200+80+7 -100-20-6

=200-100+80-20+7-6

= 100+60+1 =161

ለ. 175 — 98 = 100 + 70 + 5 — 90 — 8

ከ 5 ላይ 8 መቀነስ ስለማይቻል ከአሥር ቤት ከ 70 ላይ አንድ 10 ወስደን ከ 5 ጋር 15 ይሆናል፡፡ ከ 15 ላይ 8 ስቀነስ 7 ይሆናል፡፡ በአስር ቤት ከ 70 አንድ 10 ስለተወሰደ የቀረዉ 60 ሲሆን ከ 60 ላይ 90 መዉሰድ ስለማይቻል ከመቶ ቤት አንድመቶ ስወሰድ 160 ይሆናል፡፡ ከ 160 ላይ 90 ሲቀነስ 70 ይሆናል፡፡ ስለዚህ መልሱ 70+7= 77 ይሆናል፡፡

ሐ. 563 — 479 = __________

መ. 768 — 619 = ___________

መፍትሔ፡- ሐ. 84 መ. 149

**መልመጃ 2.2.3**

1.የሚከተሉትን ባለሦስት አሃዞችን ቀንሱ፡፡

ሀ. 124 — 115 = ____ ለ. 317 — 129 = ____

ሐ. 790 — 275 = ____ መ. 700 — 150 = ____

ሠ. 202 — 130 = ____ ረ. 840 — 638 = ____

2. የሚከተሉትን ቁልቁል ቀንሱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. 524 | ለ. 742 | ሐ. 665 |
| — 156 | — 508 | — 458 |
| _______ | _______ | _______ |
| መ. 926 | ሠ. 421 | ረ. 228 |
| —788 | —326 | —165 |
| _______ | _______ | _______ |

## 2.3. ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች

መግቢያ፡ በዚህ ርዕስ ከነባራዊ የኑሮ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች ቀርበዋል፡፡ መልመጃዎችን ለመሥራት ምሳሌዎች እንዴት እንደተሰሩ በሚገባ ተረዱ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ከመደመር እና ከመቀነስ ጋር የተያያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ፡፡

**ተግባር 2.3**

1. በአርባ ምንጭ ከተማ የሚገኘዉ የነጭ ሣር 1ኛ ደረጃ ት/ቤት በኮቪድ-19 በሽታ ምክንያት ለተማሪዎች የማስክ እደላ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ለ 1ኛ ክፍል 60 ማስኮች፤ ለ 2ኛ ክፍል 50 ማስኮች፤ ለ3ኛ ክፍል 40 ማስኮች እና ለ 4ኛ ክፍል 25 ማስኮች ቢታደሉ ጠቅላላ ለነጭ ሣር 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የታደለዉ ማስክ ብዛት ስንት ነዉ?
2. አንድ ዓሣ አስጋሪ ከሀዋሳ ሀይቅ 620 ዓሣዎችን አጠመደ፡፡ ከተጠመዱ ዓሣዎች 510 ዓሣዎችን ቢሸጥ ስንት ዓሣዎች ይቀራሉ?

ማስታወሻ፡ ጥያቄዎችን ከመሥራታችሁ በፊት በጥያቄዉ ምን እንደተሰጠ፤ ምን እንደሚጠይቅ እና የጥያቄዉን ሀሳብ በመደመር ወይም በመቀነስ እንደሚሠራ በሚገባ መረዳት አለባችሁ።

ምሳሌ 1

ሀ. አልማዝ ከሱቅ በ 100 ብር ሳሙና እና በ 250 ብር ዘይት ገዛች። በአጠቃላይ አልማዝ ያወጣችዉ ገንዘብ ስንት ነዉ?

**መፍትሔ**፡- 100+ 250 = 350ብር ነዉ።

ለ. ጌታቸዉ 500 የባህር ዛፍ ችግኞች ተከለ። ከተተከሉት ችግኞች መካከል 101 ችግኞች ቢሞቱ የፀደቁ ችግኞች ብዛት ስንት ነዉ?

**መፍትሔ**፡- 500 — 101 = 399 ችግኞች ፀደቁ

ሐ. አየለ ከገበያ 230 እንቁላል ገዝቶ ሲመጣ 20 እንቁላሎች ተሰበሩ። ስንት እንቁላሎች ይቀራሉ?

**መፍትሔ**፡- 230 — 20 =210 እንቁላሎች ይቀራሉ?

## መልመጃ 2.3

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ።

1. በአንድ ዘንቢል ዉስጥ 100 ሎሚዎች አሉ። በሌላዉ ዘንቢል ዉስጥ ደግሞ 400 ሎሚዎች አሉ። በሁለቱ ዘንቢሎች ዉስጥ ያሉ የሎሚዎች ብዛት ስንት ነዉ?
2. አበበች ከገበያ በ 200 ብር ዶሮ እና በ 25 ብር እንቁላል ገዛች። አበበች በአጠቃላይ ያወጣችዉ ብር ስንት ነዉ?
3. ወ/ሮ ገበያነሽ ከገበያ ቅቤ በ 470 ብር፣ ዶሮ በ 300 ብር እና እንቁላል በ 220 ብር ገዛች። በአጠቃላይ ወ/ሮ ገበያነሽ ያወጣችዉ የገንዘብ መጠን ስንት ነዉ?
4. የሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብርካ በመጀመሪያ ቀን 221 ሸሚዞች፤ በሁለተኛዉ ቀን 199 ሸሚዞችን አመረተ። ፋብሪካዉ በሁለት ቀናት ዉስጥ ያመረታቸዉ የሸሚዞች ብዛት ስንት ነዉ?
5. የህሊና እናት 893 ብር ይዘዉ ወደ ገበያ ሄዱ። በ 485 ብር ለልጃቸዉ ጫማ ገዝተዉ ወደ ቤታቸዉ ተመለሱ። የህሊና እናት ወደ ቤት ስንት ብር ይዘዉ ተመለሱ?
6. በመሳ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 520 ተማሪዎች ተመዝግበዋል። ከተመዘገቡት ተማሪዎች ዉስጥ 11

ተማሪዎች ቢያቋርጡ ስንት ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

እስከ 1,000 ያሉትን ቁጥሮች ለመደመር ሆነ ለመቀነስ በቅደሚያ የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚያም የ 10 እና የ 100 ብዜቶችን ለመደመርም ሆነ ለመቀነስ አሥር በአሥር ወይም መቶ በመቶ የሆኑ ዕቃዎችን መደመር እና መቀነስ ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚያም ቁጥሮችን ለመደመር ሆነ ለመቀነስ የቁጥር ቤቶችን ማወቅ እና በየቤታቸዉ በማስቀመጥ መደመር እና መቀነስ ይቻላል። በየቤቱ አስቀምጠን ስንደምር የድምር ዉጤት አሥር እና ከዚያ በላይ ከሆነ ከላይ በምሳሌዉ እንደተገለጸዉ በአለኝታ የቁጥር ቤት ዋጋ በመጠበቅ መደመር። በመቀነስ ጊዜ በየቤቱ ስናቀናንስ ተቀናሹ ከቀናሹ ከበለጠ የቁጥር ቤት ዋጋ በመጠቀም እንዴት በብድር እንደሚሰራ ከላይ በምሳሌዉ ተገልጿል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ደምሩ።

ሀ. 231 + 1 ለ. 454 + 2 ሐ. 256 + 24

መ. 960 + 30 ሠ. 325 + 446

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቀንሱ።

ሀ. 267 - 3 ለ. 483 - 24 ሐ. 989 - 271

መ. 888 - 1 ሠ. 997 — 284

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደጎን እና ቁልቁል ደምሩ።

ሀ. 64 + 34 ለ. 370 +25

ሐ.
```
  457
+  46
_____

_____
```

መ.
```
  720
 +60
_____

_____
```

4. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ

ሀ. አማረች ከሱቅ ሳሙና በ 25 ብር፤ የባትሪ ድንጋይ በ 15 ብር እና ክብሪት በ 10 ብር ገዛች። በአጠቃላይ አማረች ዕቃዎችን ለመግዛት ስንት ብር አዉጥታለች?

ለ. ከበደ አንድ የሞባይል ቀፎ በ 750 ብር ገዛ። ከበደ የገዛዉን የሞባይል ቀፎ ከሦስት ወር በኋላ በ 520 ብር ቢሸጥ በገዛበት እና በሸጠበት ምን ያህል ብር ልዩነት አለ?

ሐ. በጉጌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 480 ተማሪዎች ተመዝግበዋል። ከተመዘገቡ ተማሪዎች መካከል በሰሚስቴሩ

መጨረሻ 13 ተማሪዎች ቢያቋርጡ ስንት ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ?

መ. አቶ ታካፎ ኩሴ ታታሪ ገበሬ ነዉ፡፡ በዓመት 120 ኩንታል በቆሎ፤ 20 ኩንታል ጤፍ እና 6 ኩንታል ባቄላ ቢያገኝ በአጠቃላይ አቶ ታካፎ ኩሴ በዓመቱ ስንት ኩንታል ምርት አገኘ?

# ምዕራፍ 3

## እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ማባዛት

መግቢያ፡ በቅድሚያ በረድፍ የተቀመጡ ዕቃዎችን ብዛታቸዉን ለማወቅ ወደ ማባዛት ዐረፍተ ነገር መቀየር፡፡ የአሥር ብዜቶችን ከዚህ ቀደም ስለተማራችሁ የ 10 ብዜቶችን በማስታወስ እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች ከ 1 በመጀመር እስከ 9 ካሉ ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ጋር እንዴት እንደሚባዙ ከምሳሌዎች በመረዳት መልመጃዎችን መስራት

የትምህርቱ ዓላማዎች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የማባዛትን ጽንሰ ሀሳብ ትረዳላችሁ፡፡
- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ጋር ታባዛላችሁ፡፡

## 3.1. እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 ማባዛት

መግቢያ፡ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮች እንዴት በ 2 እንደምባዙ በሠንጠረዥ እና በሥዕል ማብራሪያዎች ስለተሰጠ ቀጥሎ ያሉ ተግባራትን እና ምሳሌዎችን በመሥራት መልመጃዎችን መስራት ትችላላችሁ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 ታባዛላችሁ፡፡

### ተግባር 3.1

1. የሚከተሉትን እዉነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. 8 + 8 = 16

ለ. 8 + 8 ማለት 8 ን ሁለት ጊዜ መደመር ማለት ነዉ፡፡

ሐ. 8 + 8 እና 8 × 2 እኩል ናቸዉ፡፡

2. በሚከተለዉ ሣጥን ዉስጥ ስንት አሣዎች አሉ? የአሣዎችን ብዛት ለማግኘት በማባዛት ዐ.ነገር መጻፍ እንዴት ይቻላል?



2 + 2 + 2 + 2 + 2 + 2 + 2 + 2 = ____

_____ × _______ = __________

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. አየለ በየቀኑ ዕንቁላል የሚጥሉ 16 ዶሮዎች ቢኖሩት በሁለት ቀን ዉስጥ ስንት ዕንቁላሎችን ያገኛል?

ለ. 10 × 2 ስንት ይሆናል?

ማስታወሻ፡ ማባዛት ማለት አንድን ቁጥር ደጋግሞ ከመደመር ጋር ይዛመዳል።ተማሪዎች የማባዛት ምልክት "×" ይህንን ይመስላል። አንድን ቁጥር በ 2 ማባዛት ማለት ያንን ቁጥር ሁለት ጊዜ መደመር ማለት ነዉ።

ምሳሌ 1. የኳሶችን ብዛት ጻፉ።



ለ.



ሀ. 2 × 1 = _____

ለ. 2 × 2 = _____

 ሐ. 2 × 3 = _____

መፍትሔ

ሀ.  ለ. 

2 × 1 = 2      2 × 2 = 4

 ሐ. 2 × 3 = 6

ምሳሌ 2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሳቸዉን በባዶ ቦታ ላይ ጻፉ፡፡

ሀ. 2 × 1 = _______      ለ. 2 × 2 = _______

ሐ. 2 ×12 = _______      መ. 2 × 15 = _______

መፍትሔ ሀ. 2 × 1 = <u>2</u>      ለ. 2 × 2 = <u>4</u>

ሐ. 2 × 12 = <u>24</u>      መ. 2 × 15 = <u>30</u>

## መልመጃ 3.1

1.የኳሶችን ብዛት ጻፉ፡፡

ሀ.  2 x 1 = ________

ለ.  2 x 2 = _____________

ሐ.  2 x 3 = _____

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሳቸዉን በባዶ ቦታ ላይ ጻፉ፡፡

ሀ. $2 \times 2 =$ _______ ለ. $2 \times 3 =$ _______

ሐ. $2 \times 6 =$ _______ መ. $2 \times 10 =$ _______

ሠ. $2 \times 8 =$ _______

3. ከሚከተሉት ቁጥሮች መካከል የሁለት ብዜት ያልሆኑ ቁጥሮች የትኞች ናቸዉ?

ሀ. 4፣ 5፣ 10፣ 11፣ 15፣ 18

## 3.2. እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ 10 ማባዛት

መግቢያ፡ እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 ማባዛት ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ 10 እንዴት እንደምታባዙ በምሳሌ የተገለጸ ስለሆነ በጥንቃቄ በማንበብ መልመጃዎችን መስራት አለባችሁ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ 2 እና በ 10 ታባዛላችሁ፡፡

## ተግባር 3.2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን ተወያዩ፡፡

   ሀ. $2 \times 1 =$ _______ ለ. $2 \times 30 =$ _______

   ሐ. $2 \times 10 =$ _______ መ. $2 \times 20 =$ _______

   ሠ. $2 \times 45 =$ _______ ረ. $2 \times 99 =$ _______

2. ትክክለኛዉን መልስ በባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

ሀ. $10 \times 1 =$ _______ ለ. $10 \times 2 =$ _______

ሐ. $10 \times 5 =$ _______ መ. $10 \times 9 =$ _______

ሠ. $10 \times 10 =$ _______ ረ. $10 \times 11 =$ _______

ሰ. $10 \times 20 =$ _______ ሽ. $10 \times 45 =$ _______

ቀ. $10 \times 99 =$ _______

3. በ 6 እና በ12 መካከል የሚገኙ የሁለት ብዜቶችን ጻፉ፡፡

4. ከ 1 እስከ 100 ድረስ ያሉትን የአሥር ብዜቶች ጻፉ፡፡

5. ከ 20 እስከ 100 ድረስ ያሉትን የሁለት ብዜቶች ጥሩ።

ማስታወሻ

- አንድን ቁጥር በሁለት ማባዛት ማለት ቁጥሩን ሁለት ጊዜ መደመር ማለት ሲሆን በአሥር ማባዛት ማለት ደግሞ አንድን ቁጥር አሥር ጊዜ መደመር ማለት ነዉ።

ምሳሌ. 1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ።

ሀ. 2 × 3 = _______ ለ. 2 × 4 = _______

ሐ. 2 × 50 = ______ መ. 2 × 12 = _______

ሠ. 2 × 30 = _______

**መፍትሔ**

ሀ. 2 × 3 = 6 ለ. 2 × 4 = 8

ሐ. 2 × 50 = 100 መ. 2 × 12 = 24

ሠ. 2 × 30 = 60

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ።

ሀ. 2 × 10 = _______ ለ. 3 × 10 = _______

ሐ. 5 × 10 = _______ መ. 4 × 10 = _______

ሠ. 9 × 10 = _______

**መፍትሔ**

ሀ. 2 × 10 = 20 ለ. 3 × 10 = 30

ሐ. 5 × 10 = 50 መ. 4 × 10 = 40

ሠ. 9 × 10 = 90

3. የሚከተሉትን የ 2 እና የ 10 ብዜት ሠንጠረዦችን አንብቡአቸዉ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | 2 | 4 | 6 | 8 | 10 |

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 |

**መልመጃ 3.2**

1.የሚከተሉትን የሁለት ብዜቶች በማባዛት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡

ሀ. 2 × 3 = _______ ለ. 2 × 8 = _______

ሐ. 2 × 24 =______ መ. 2 × 50 = ______

ሠ. 2 × 40 =______

2. የሚከተሉትን የአሥር ብዜቶችን በማባዛት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ።

ሀ. 10×2 = ______ ለ. 10×6 = ______

ሐ. 10×7 =______ መ. 10×8 =______

ሠ. 10× 9 =______

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች በማባዛት መልሳቸዉን በጎደሉ ቦታዎች ሙሉአቸዉ።

ሀ. 2 × 28 = ______ ለ. 2 × 27 =______

መ. 10 × 1 =______ ሠ. 10 × 5 =______

4. በባዶ ቦታዎች ዉስጥ የሚገቡ ሙሉ ቁጥሮችን ፈልጉ።

ሀ. ___ × 3 = 30 ለ. ___ × 4 = 40

ሐ.___ × 5 = 50 መ. ___×2 = 18

ሠ. ___ ×2 = 42

5. ከሚከተሉት ቁጥሮች ዉስጥ የ 2 ብዜቶችን በመክበብ ለዩ::

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ. | 42 | 45 | 24 | 6 | 7 | 69 | 75 | 82 |
| ለ. | 5 | 7 | 9 | 10 | 12 | 13 | 16 | 33 |
| ሐ. | 52 | 54 | 56 | 57 | 58 | 59 | 60 | 61 |

6. ከሚከተሉት ቁጥሮች ዉስጥ የ 10 ብዜቶችን በመክበብ ለዩ::

15 20 25 30 35 40 45 50 55 60

## 3.3. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 1 ማባዛት

**መግቢያ:** እስከ 100 ያሉ ቁጥሮች በ 1 እንዴት እንደሚባዙ ምሳሌዎች የቀረቡ ስለሆነ በምሳሌዉ መሠረት መልመጃዎችን ሥሩአቸዉ::

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት:-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-**

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 1 ታባዛላችሁ::

## ተግባር 3.3

1. ሙሉ ቁጥሮች ከ 1 ጋር ሲባዙ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይችላል? ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡
2. ማንኛዉም ሙሉ ቁጥር በ 1 ማባዛት ሙሉ ቁጥሩን ይቀይረዋል? ወይስ አይቀይረዉም? በቡድን ተወያዩ፡፡

ማስታወሻ፡ ማንኛዉንም ቁጥር በ 1 ስናባዛ የምናገኘዉ መልስ ቁጥሩ ራሱን ነዉ፡፡

ምሳሌ 1 የሚከተሉትን የማባዛት ጥያቄዎች ሥሩ፡፡

ሀ. $1 \times 2 =$ ______ ለ. $1 \times 8 =$ ______

ሐ. $1 \times 40 =$ ______ መ. $1 \times 100 =$ ______

**መፍትሔ** ሀ. $1 \times 2 = \underline{\underline{2}}$ ለ. $1 \times 8 = \underline{\underline{8}}$

ሐ. $1 \times 40 = \underline{\underline{40}}$ መ. $1 \times 100 = \underline{\underline{100}}$

ምሳሌ 2. በየረድፍ ያሉ ኩባያዎች እንዴት በ 1 በማባዛት ወደ ማባዛት ዐረፍተ ነገር መለወጥ እንደሚቻል ከዚህ በታች ባለዉ ሥዕል ላይ ተመልክቷል፡፡



1 x 1 = 1

2 x 1 = 2

3 x 1 = 3

4 x 1 = 4

5 x 1 = 5

6 x 1 = 6

ምሳሌ 3 ከዚህ በታች ባለዉ ሠንጠረዥ ዉስጥ የጎደሉ ባዶ በታዎችን ሙሉ፡፡

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | 2 | | | | 6 | | | 9 | |

ምሳሌ 4



$$1 \times 6 = 6$$

## መልመጃ 3.3

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታ ሙሉ፡፡

ሀ.

| | |
|---|---|
|  | _____ x ______ = ____ |
|  | _____ x ______ = ____ |
|  | _____ x ______ = ____ |

ለ. 

$1 \times 8 =$ ___

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ፡፡

ሀ. $1 \times 6 =$ ___ ለ. $1 \times 23 =$ ___

ሐ. $1 \times 99 =$ ___ መ. $1 \times 5 =$ ___

3. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. $1 \times 15 =$ ______ ለ. $95 \times 1 =$ ______

ሐ. $4 \times 1 =$ ______ መ. $84 \times 1 =$ ______

## 3.4. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ማባዛት

**መግቢያ፡** ከዚህ በፊት እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 1 በ 2 እና በ10 ማባዛት ተምራችኋል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና በ 9 እንዴት እንደሚባዙ በቅደም ተከተል ትማራላችሁ።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ታባዛላችሁ።

ማስታወሻ፡ አንድን ቁጥር በ 3 ማባዛት ማለት ቁጥሩን ሦስት ጊዜ ደጋግሞ መደመር፤ በ 4 ማባዛት ማለት ቁጥሩን አራት ጊዜ ደጋግሞ መደመር፤ በዚህ መሠረት 9 ጊዜ ማባዛት ማለት ቁጥሩን ዘጠኝ ጊዜ ደጋግሞ መደመር ማለት ነዉ።

### 3.4.1 በሦስት ማባዛት

**ተግባር 3.4.1**

1. እስከ 10 ያሉ የ 3 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን መናገር ትችላላችሁ?
2. በቁጥር መስመር ላይ ከ 3 በመጀመር ሦስት ሦስት እየቆጠራችሁ እስከ 20 ድረስ የምታገኙአቸዉን ቁጥሮች ጻፉ።
3. የ 3 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን ከ 20 እስከ 30 ያሉትን ጻፉ።
4. 17 የ 3 ብዜት ነዉ?

ማስታወሻ፡ ከ 1 እስከ 100 ካሉ ቁጥሮች ዉስጥ ወይም በቁጥር መስመር ላይ ከ 3 ጀምረን ሦስት ሦስት በመዝለል




የምናገኛቸዉ ቁጥሮች የ 3 ብዜት ናቸዉ።

**ምሳሌ**

1. የሚከተሉትን ምሥሎች ብዛት ለማግኘት እንዴት ወደ ማባዛት ዐረፍተ ነገር እንደተቀየረ ተረዱ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ◈◈◈ | $1 \times 3 = 3$ | | | |
| ◈◈◈ | ◈◈◈ | $2 \times 3 = 6$ | | |
| ◈◈◈ | ◈◈◈ | ◈◈◈ | $3 \times 3 = 9$ | |
| ◈◈◈ | ◈◈◈ | ◈◈◈ | ◈◈◈ | $4 \times 3 = 12$ |

2. የሚከተሉትን ሠንጠረዦች በማየት አንብቡ።

ሀ.



ለ.



መፍትሔ ሀ. $3 \times 1 = 3$

ለ. $3 \times 4 = 12$

3. ምድቦች እያንዳንዳቸዉ 3 እንቁላሎች አሏቸዉ፡፡ ስለዚህ የእንቁላሎች ብዛት ስንት ነዉ?



3 × 3 = __9_

4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ፡፡

ሀ. 3+3+3+3 = 3 x 4 = 12

ለ. 3+3+3+3+3+3+3 = 3 x 7 = 21

ሐ. 3+3+3+3+3+3+3+3+3+3+3 = 3 x 11 = 33

5. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

ሀ. _____ × 3 = 6　　ለ. ______ × 3 = 9

ሐ. ______ × 3 = 30　　መ. ______ × 3 = 18

ሠ. _____ × 3 = 12

**መፍትሔ**

ሀ. _2_ × 3 = 6　　ለ. 3_ × 3 = 9

ሐ. _10_ × 3 = 30　　መ. _6_ × 3 = 18

ሠ. _4_ × 3 = 12

## መልመጃ 3.4.1

1. በምሥሉ ያሉ ችግኞች ብዛት ስንት ነዉ?

$2 \times 6 =$ _____



2. የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ. $3 \times 1 =$ ______

ለ. $3 \times 5 =$ ______

ሐ. $3 \times 20 =$ _____

መ. $3 \times 8 =$ _____

ሠ. $3 \times 12 =$ ______

3 . በሚከተለዉ ምሥል የመቀሶች ብዛት ስንት ነዉ?



_____ × _____ = _____

4. ቀጥሎ ባሉ ክፍት ቦታዎች የሚገቡ ቁጥሮችን ጻፉ።

ሀ. 3 × ______= 24 ለ. 3 × ______ = 12

ሐ. 3 × ______ = 42 መ. 3 × ______ = 36

ሠ. 3 × ______ = 30

## 3.4.2. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 4 እና በ 5 ማባዛት

ተግባር 3.4.2

1. ከ 1 እስከ 20 ካሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ 4 ብዜቶችን ጻፉ።
2. ከአንድ እስከ 30 ካሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ 5 ብዜቶችን ጻፉ።
3. የ 4 ብዜቶች በሙሉ የ 5 ብዜት ሊሆኑ ይችላሉ? ተወያዩበት
4. እስከ 50 ካሉ ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ 4 ብዜት የሆኑ እና የ 5 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች እነማን ናቸዉ? በቡድን ተወያዩበት።

ማስታወሻ፡ ከ 4 ጀምረን አራት አራት በመዝለል ስንቆጥር የምናገኘዉ የ 4 ብዜቶችን ሲሆን ከ 5 ጀምረን አምስት

## አምስት በመዝለል ስንቆጥር የምናገኛቸዉ የ 5 ብዜቶችን ነዉ፡፡

ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብቡ፡፡

ሀ.



የኳሶች ብዛት ስንት ነዉ?______

5 × 4 = 20

ለ.

ሀ. 4 × 1 = 4 ለ. 4 × 2 = 8

ሐ. 5 × 1 = 5 መ. 4 × 10 = 40

ሠ. 4 × 11 = 44 ረ. 5 × 6 = 30

ምሳሌ 2. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

ሀ  ______ x ______ = _____

ለ  ______ x ______ = _____

ሐ  ______ x ______ = _____

መ  ______ x ______ = _____

መፍትሔ፡ ሀ. 4 × 1 = 4 ለ. 4 × 2 = 8

ሐ. 5 × 1 = 5 መ. 5 × 2 = 10

**መልመጃ 3.4.2**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ፡፡

ሀ. 4 × 3 = _____ ለ. 4 × 9 = _____

ሐ. 4 × 13 = _____ መ. 4 × 4 = _____

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ፡፡

ሀ. 5 × 2 = _____ ለ. 5 × 10 = _____

ሐ. 5 × 14 = _____ መ. 5 × 13 = _____

3. ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡

ሀ  ____ x ____ = ____

ለ  ____ x ____ = ____

ሐ  ____ x ____ = ____

መ  ____ x ____ = ____

4. ሰይድ 10 ፍየሎች አሉት፡፡ የ 10 ፍየሎች እግር ብዛት ስንት ይሆናል?
5. ወርቅነሽ 20 የቡና ችግኝ መደብ አዘጋጅታለች፡፡ በእያንዳንዱ መደብ አምስት አምስት ችግኞች ብትተክል ወርቅነሽ በጠቅላላዉ የተከለችዉ የቡና ችግኞች ብዛት ስንት ነዉ?

### 3.4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 6 እና በ 7 ማባዛት

ተግባር 3.4.3

1. እስከ 100 ያሉ የ 6 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?
2. እስከ 100 ያሉ የ 7 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?
3. የ 6 ብዜቶች የ 2 ብዜቶች መሆን ይችላሉ?
4. የ 6 ብዜቶች የ 3 ብዜቶች መሆን ይችላሉ?
5. የ 6 ብዜቶች የ 2 እና የ 3 ብዜቶች መሆን ይችላሉ?

6. ከ 20 እስከ 42 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ 7 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?

7. ከ 40 እስከ 50 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ 6 እና የ 7 ብዜቶች ሊሆኑ የሚችሉ ሙሉ ቁጥሮች አሉ? እነማን ናቸዉ?

**ምሳሌ፡**

1. የሚከተሉትን ምሳሌዎች አንብቡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. 6 × 1 = 6 | ለ. 6 × 2 = 12 |
| ሐ. 6 × 5 = 30 | መ. 6 × 10 = 60 |
| ሠ. 7 × 2 = 14 | ረ. 7 × 7 = 49 |
| ሰ. 7 × 10 = 70 | ሸ. 7 × 11 = 77 |

2. የሚከተሉትን ምሥሎች ብዛት ለማግኘት ወደ ማባዛት ዐረፍተ ነገር በመቀየር ብዛታቸዉን ፈልጉ፡፡

ሀ.



6 × 3 = ________

ለ.



$5 \times 6 =$ ________

ሐ.



$7 \times 1 =$ ___



መ. $7 \times 3 =$ ________

መፍትሔ፡ ሀ. 18 ለ. 36

ሐ. 7 መ. 21

3. የሚከተሉትን በምሳሌዉ መሠረት ሥሩ፡፡

ምሳሌ-1 6+6+6+6 = 6 × 4 = 24

ሀ. 7+7+7+7+7+7+7= ______

ለ. 6+6+6+6+6+6+6+6+6+6 = ______

መፍትሔ፡- ሀ. 7 × 7 = 49 ለ. 6 × 10 = 60

ምሳሌ-2




6 x 7 = (6 x 3) + (6 x 4)

= 18 + 24

= 42

ሐ.




___ x ___ = ( ___ x ___) + (___ x ___)

= ___ + ___

= ___

መ.




___ x ___ = ( ___ x ___) + (___ x ___)

= ___ + ___

= ___

መፍትሔ፡- ሐ. 6 x 7 = 42

= (6 x 2) + (6 x 5)

= 12 + 30

= 42

መ. 6 x 5 = 30

= (6 x 2) + (6 x 3)

= 12 + 18

= 30

4. የሳጥኖችን ዋጋ ሊተካ የሚችለዉን ሙሉ ቁጥሮችን ሙሉ፡፡

ሀ. ☐ × 7 = 49

ለ. ☐ × 6 = 30

ሐ. ☐ × 7 = 42

መ. ☐ × 6 = 72

መፍትሔ፡- ሀ. 7 ለ. 5 ሐ. 6 መ. 12

## መልመጃ 3.4.3

1. የሚከተሉትን ሠንጠረዦች በማየት በዉስጡ ያለዉን የካሬ ብዛት በመቁጠር ወደ ማባዛት በመቀየር የጎደለዉን ሙሉ።

ሀ.  ___ × ___ = ____

ለ.  ____ × ____ = ______

ሐ.  ____ × _____ = ______

2. የሚከተሉትን የማባዛት ጥያቄዎችን ሥሩ።

ሀ. 6 × 1 = ________ ለ. 6 × 5 = _________

ሐ. 6 × 8 = _________ መ. 6×10 = _________

ሠ. 6×11 = _________ ረ. 6 × 99 = _________

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ።

ሀ. $7 \times 4 =$ __________ ለ. $8 \times 7 =$ __________

ሐ. $7 \times 9 =$ __________ መ. $7 \times 10 =$ __________

ሠ. $7 \times 11 =$ __________ ረ. $7 \times 77 =$ __________

4. ወ/ሮ አየለች 7 ልጆችን ታስተምራለች። ለእያንዳንዳቸዉ 8 ደብተሮች ብትገዛ ወ/ሮ አየለች በአጠቃላይ ስንት ደብተሮች ገዛች?

5. በ 10 እና በ 50 መካከል ስንት የ 7 ብዜቶች አሉ?

6. በሚከተሉት ጥያቄዎች ዉስጥ ያሉ ባዶ ቦታዎችን ሙሉ

ሀ .



ለ



## 3.4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 8 እና በ 9 ማባዛት

ተግባር 3.4.4

1. እስከ 100 ያሉ የ 8 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?
2. እስከ 100 ያሉ የ 9 ብዜቶች እነማን ናቸዉ?
3. የ 8 ብዜቶች ሁሉ የ 4 ብዜቶች ናቸዉ?
4. ሁሉም የ 9 ብዜቶች የ 3 ብዜቶች ናቸዉ? ተወያዩባቸዉ።

5. በ1 እና በ 80 መካከል የሚገኙ የ 8 እና የ 9 ብዜቶችን ጻፉ፡፡

ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ብዜቶችን አንብቡ፡፡

ሀ. 8×7 = 56 ለ. 9×9 = 81 ሐ. 8×3 = 24

መ. 8×2 = 16 ሠ. 9 ×5 = 45 ረ. 9×1 = 9

ምሳሌ 2



9 × 4 = 36

<u>ምሳሌ 3፡ የሚከተሉትን አስሉ፡፡</u>

ሀ. 8+8+8+8+8+8+8 = 8 × 7 = 56

ለ . 8+8+8+8+8+8 = 8 × 6 = 48

ሐ. 9+9+9+9+9 = 9 × 5 = 45

መ. 9+9+9+9+9+9+9+9+9 = 9 × 9 = 81

## መልመጃ 3.4.4

1. ለሚከተሉት የማባዛት ጥያቄዎች መልሳቸዉን ፈልጉ፡፡

ሀ. 8 × 15 =______ ለ. 8 × 22 =______

ሐ. 8 × 31 =______ መ. 8 × 46 =______

ሠ. 8 × 87 =_____ ረ. 8 × 95 =_____

2. ለሚከተሉት የማባዛት ጥያቄዎች መልሳቸዉን ፈልጉ።

ሀ. 9 × 13 =_____ ለ. 9 × 24 =_____

ሐ. 9 × 57 =_____ መ. 9 × 69 =_____

ሠ. 9 × 71 =_____ ረ. 9 × 80 =_____

3. በሚከተለዉ የቁጥር መስመር የጎደለዉን ቁጥር ሙሉ።

ሀ.



ለ



4. የአልማዝ ዕድሜ 8 ነዉ። የአባቷ ዕድሜ የአልማዝን ዕድሜ አራት እጥፍ ቢሆን የአልማዝ አባት ዕድሜ ስንት ነዉ?

5. ባዶ ቦታዎችን የሚወክሉ ሙሉ ቁጥሮችን ሙሉ።

ሀ. 8፣ 16፣_____ ፣ 32፣ _____፣ 48 ፣_____፣ _____

ለ. _____፣ 18፣_____ ፣ 36፣ 45፣ 54 ፣_____፣ 72

## 3.5. የቃላት ፕሮብሌሞች

**መግቢያ፡** በዚህ ንዑስ ርዕስ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 እንዴት እንደሚባዙ ስለተማራችሁ ይህንን ሀሳብ በቃላት ፕሮብሌሞች እንዴት ተጠቅማችሁ መሥራት እንዳለባችሁ በምሳሌዎች የተገለጸ ስለሆነ ምሳሌዎችን በመረዳት መልመጃዎችን ሥሩ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የሚያካትቱ የቃላት ፕሮብሌሞችን ማባዛት እና ማካፈልን በመጠቀም ትፈታላችሁ፡፡

**ተግባር 3.5**

1. አቶ ዱቡሻ ለ 5 ልጆች ለእያንዳንዳቸዉ 6 የማንጎ ፍሬዎችን ቢሰጥ በጠቅላላዉ ስንት የማንጎ ፍሬዎችን ሰጠ?
2. አቶ አድማሱ 8 ልጆችን ይረዳሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ልጅ 6 ደብተሮች ቢገዛ በጠቅላላ ስንት ደብተሮችን ገዛላቸዉ?

3. በዛይሴ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ1ኛ እና በ 2ኛ ክፍል በእያንዳንዱ 40 ተማሪዎች በ 3ኛ እና 4ኛ ክፍል በእያንዳንዱ 35 ተማሪዎች አሉ፡፡ በትምህርት ቤቱ ከ 1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ስንት ተማሪዎች አሉ?

ማስታወሻ፡ የቃላት ፕሮብሌም ለመሥራት መጀመሪያ ምን እንደተሰጠ እና እንደተጠየቀ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም የሚሰራበትን ዘዴ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ

1. የኮንሶ ማዘጋጃ ቤት ለ 10 አገር መከላከያ ጡረተኞች የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ለእያንዳንዱ 100 ካሬ ሜትር ቦታ ቢሰጣቸዉ በአጠቃላይ ማዘጋጃዉ ለአገር መከላከያ ጡረተኞች የሰጠዉ መሬት ስንት ካሬ ሜትር ነዉ?

2. በክልላችን በሚገኘዉ በጉጌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ 1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል 60 መጻህፍት በሽልማት ተሰጡ፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍል እኩል የሚከፋፈል ቢሆን ለእያንዳንዱ ክፍል ምን ያህል መጻህፍት ይደርሳቸዋል?
3. የአንድ እስክርብቶ ዋጋ 10 ብር ቢሆን በ 90 ብር ስንት እስከርብቶዎችን መግዛት ይቻላል?

4. አቶ ዳሞሼ የዶሮ አርቢ ሲሆኑ በበዓል ወቅት በጎረቤት ላሉ ለ 5 አቅመ ደካማ ቤተሰቦች 20 እንቁላሎችን እኩል ቢያከፋፍሉ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ምን ያህል እንቁላል ይደርሳቸዋል?

## መፍትሔ

1. 1000 ካሬ ሜትር 2. 10 መጻህፍት 3. 9 እስክርብቶ

4. 4 እንቁላል

## መልመጃ 3.5

1. ማንኛዉንም ሙሉ ቁጥር በ 1 ማባዛት እና ለ 1 ማካፈል ሙሉ ቁጥሩን ይቀይረዋል? ወይስ አይቀይረዉም?
2. ከ 1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሽልማት ተዘጋጀ። ከእያንዳንዱ ክፍል በደረጃቸዉ የሚሸለሙ ሦስት ሦስት ተማሪዎች ቢሆኑ በጠቅላላ የሚሸለሙ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነዉ?
3. አቶ ተሰማ እያንዳንዱ መደብ 8 የእንሰት ችግኞችን የሚይዝ መደብ አዘጋጀ ። የመደቦች ብዛት 7 ቢሆን በአጠቃላይ መደቦች ስንት የእንሰት ችግኞችን መትከል ይቻላል?

4. የአንድ ደብተር ዋጋ 5 ብር ነዉ። በ 40 ብር ስንት ደብተሮችን መግዛት ይቻላል?

5. አንድ የህብረት ሥራ ማህበር እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን ገዝቶ ለ 10 የማህበሩ አባላት ለእያንዳንዱ 30 ዶሮዎችን አከፋፈለ። በጠቅላላ ያከፋፈላቸዉ የዶሮዎች ብዛት ስንት ነዉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ፡

ቁጥሮችን በአንድ ስናባዛ የሚናገኘዉ መልስ የተሰጠዉ ቁጥር ራሱ ይሆናል። ቁጥሮችን በ 2 ማባዛት ማለት የተሰጠዉን ቁጥር ሁለት ጊዜ መደመር ማለት ነዉ።በዚህ ዓይነት በ 3፤4፤5፤6፤7፤ 8 እና 9 ማባዛት ማለት ቁጥሮችን በተሰጠዉ ብዜት ልክ መደመር ማለት ነዉ።

### የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ።

ሀ. 3 ×2 =______

ለ. 3 ×6 =______

ሐ. 8 × 7 =______

መ. 9 × 9 =______

ሠ. 5 × 10 =______

ረ. 4 × 11 =______

ሰ. 3 × 47 =______

ሸ. 8 × 85 =______

ቀ. 9 × 76 =______

2. በሚከተሉት ጥያቄዎች የጎደሉ ቦታዎችን የሚወክሉ ቁጥሮችን ሙሉ።

ሀ. 4፣ 8፣_____ ፣ 16፣ _____፣ 24 ፣_____፣ _____

ለ. _____፣ 10፣_____ ፣ 20፣ _____፣ _____፣_____

ሐ. 7፣ _____፣21 ፣ 28፣ _____፣_____፣ _____

3. በሚከተሉት ሠንጠረዦች ውስጥ ያሉ ካሬዎችን በመቁጠር እና ወደ ማባዛት በመለወጥ ብዛታቸውን ጻፉ።

ሀ.



_____ × _____ =_____

ለ.



_____ × _____ =______

ሐ.



____ × ____ =____

= (__ x__) + (__ x __)

= ___ + ___

= ___

መ.



____ × ____ =_____

= (__ x__) + (__ x __)

= ___ + ___

= ___

4. በሳጥኑ ውስጥ መግባት ያለባቸዉን ሙሉ ቁጥሮች ፈልጉ፡፡

ሀ. ☐ × 6 = 24 ለ. ☐ × 7 = 42

ሐ. 8 × ☐ = 72 መ. ☐ × 9 = 90

5. በ 21 እና በ 51 መካከል የሚገኙ የ አራት ብዜቶች በቅደም ተከተል ዘርዝሩ፡፡

6. ከ 1 እስከ 50 ካሉ ቁጥሮች መካከል የሚከተሉትን ቁጥሮች ብዜት ጻፉ፡፡

ሀ. የ 3 ብዜት______________________________

ለ. የ 4 ብዜት______________________________

ሐ. የ 5 ብዜት____________________________

መ. 6 ብዜት______________________________

ሠ. የ 7 ብዜት_____________________________

ረ. የ 8 ብዜት_____________________________

ሰ. የ 9 ብዜት_____________________________

7. ደበበ መጽሐፍ ማንበብ ይወዳል፡፡ 250 ገጾች ያሉት አንድ መጽሐፍ ሲያነብ በቀን 10 ገጾችን ማንበብ ከቻለ መጽሐፉን አንብቦ ለመጨረስ ምን ያህል ቀን ያስፈልገዋል?
8. አንድ ገበጣ 12 ጉድጓዶች አሉት፡፡ በእያንዳንዱ ጉድጓድ 4 ጠጠሮች ቢኖሩ በጠቅላላ በገበጣዉ ጉድጓዶች ዉስጥ ስንት ጠጠሮች ይገኛሉ?

# ምዕራፍ 4

## ግማሽ እና ሩብ

**መግቢያ፡-** በዚህ ርዕስ የግማሽ እና ሩብ ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ሥዕሎች እና ምሳሌዎች ስለቀረቡ ተግባራትን እና ምሳሌዎችን በሚገባ ሥሩ፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በግማሽ እና በሩብ መክፈልን ትረዳላችሁ፡፡
- ግማሽ እና ሩብን በቁጥር መስመር ታሳያላችሁ፡፡

## 4.1. ግማሽ

**መግቢያ፡-** በዚህ ርዕስ አንድ ዕቃ ወይም ስብስቦችን በግማሽ እንዴት እንደሚከፈሉ በሥዕልና በምሳሌ የተገለጸ ስለሆነ የቀረቡ ተግባራትን እና ምሳሌዎችን በጥንቃቄ ይሰራሉ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የእኩል ማካፈልን ጽንሰ ሀሳብ ትለያላችሁ፡፡
- አንድ የተሰጠ ሙሉ ነገር ለግማሽ ትከፍላላችሁ፡፡
- ግማሽን በተለያዩ መንገዶች ትገልጻላችሁ፡፡

### ተግባር 4.1

1. አንድ ወረቀት በመዉሰድ ጫፍ እና ጫፋቸዉን በማገናኘት እጠፉት፡፡ ያጠፋችሁትን ወረቀት ከታጠፈበት ቦታ ላይ ቁረጡት፡፡ ያገኛችሁት ቁራጭ ወረቀት ከመጀመሪያዉ ወረቀት ጋር አወዳድሩ፡፡
2. ለሁለት ተማሪ አንድ ሙሉ ዳቦ ቢሰጣቸዉ እንዴት ነዉ የምከፋፈሉት?

ማስታወሻ፡- ግማሽ ማለት አንድን ሙሉ ዕቃ ወይም የዕቃዎችን ክምችት ለሁለት እኩል ቦታ ሲካፈል የሚገኘዉ እያንዳንዱ ክፍል ግማሽ ይባላል፡፡




ምሳሌ.1 ፡-ከዚህ በታች ያለዉ እንጀራ በሁለት ቦታ እኩል የተከፈለ ነዉ፡፡ የተቀባዉ እና ያልተቀባዉ ክፍል እኩል ናቸዉ፡፡ ስለዚህ የተቀባዉ ክፍል ከአጠቃላዩ ክፍል ጋር ሲወዳደር ግማሽ ይባላል፡፡ ይህም ሲነበብ ግማሽ እንላለን፡፡

ሙሉ እንጀራ



እንጀራ ሲታጠፍ



ምሳሌ.2. አንድ የዉሃ መያዣ 20 ሊትር ዉሃ ይይዛል፡፡ የዉሃ መያዣዉ ግማሽ ስንት ሊትር ይሆናል?

መፍትሔ፡ 10 ሊትር ዉሃ ይይዛል፡፡



ምሳሌ 3፡- ከዚህ በታች ባለዉ የቁጥር መስመር ላይ ከ 0 እስከ 1 ያለዉ ሙሉ ከሆነ የተቀባዉ ክፍል ምን ይባላል?




**መፍትሔ፡** ግማሽ ነዉ፡፡

**መልመጃ 4.1**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ደብተራችሁ ላይ በመጻፍ መልሱ

ሀ.  የተቀባዉ ክፍል ____________ ነዉ.

ለ.  የተቀባዉ ክፍል ____________ ነዉ.

ሐ. በቁጥር መስመር ላይ የተቀባዉ ከ 0 እስከ 1 ላለዉ ክፍል ምን ይባላል?




1.

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

ሀ. አንድ ሙሉ ስንት ግማሾች አሉት?

ለ. አንድ ሙሉ ለሁለት ብከፈል እያንዳንዱ ክፍል ምን ይባላል?

ሐ. አራት ግማሾች ስንት ሙሉ ናቸዉ?

መ. አንድ ዳቦ እኩል ብንከፍለዉ ስንት ቦታ ይከፋፈላል?

ሠ. አበበ እና አየለ ወንድማማቾች ናቸዉ፡፡ እናታቸዉ ለሁለቱ አንድ ብርቱኳን ብትሰጥና ለአበበ የብርቱኳኑ ግማሽ ብደርሰዉ የአየለ ድርሻ ምን ያህል ነዉ?

ረ. የሚከተሉትን ሥዕሎች ግማሽ ቀቡ፡፡



## 4.2. ሩብ

**መግቢያ፡** በዚህ ርዕስ አንድን ዕቃ ወይም ስብስቦች በሩብ እንዴት እንደሚከፋፈሉ በሥዕልና በምሳሌ የተገለጸ ስለሆነ ተግባራትን እና ምሳሌዎችን በሚገባ ተረዱ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- አንድ የተሰጣችሁን ሙሉ ነገር በሩብ ትከፍላላችሁ፡፡
- አንድ የተሰጣችሁን የዕቃዎች ክምችት ለሩብ ትከፍላላችሁ፡፡
- የሩቦች እና የአንድ ሙሉን ዝምድና ትገነዘባላችሁ፡፡

**ተግባር 4.2**

1. አንድ ብርትኳን አራት እኩል ቦታ ብንከፍለዉ እያንዳንዱ ክፍል ምን ይባላል?
2. በአንድ ግማሽ ዉስጥ ስንት ሩቦችን እናገኛለን?

3. አንድ እንጀራ ሁለት ጊዜ በእኩል ብታጥፉት እና ብትቆርሱት እያንዳንዱ ቁርጥራጭ ምን ይባላል?

ማስታወሻ፡- አንድን ሙሉ ነገር አራት እኩል ቦታ ብንከፍለዉ እያንዳንዱ ክፍል ሩብ ይባላል፡፡

## ምሳሌ

1. በሚከተሉት ምሥሎች ዉስጥ የተቀባዉን መጠን ጻፉ፡፡

ሀ.  የተቀባዉ ክፍል ሩብ ነዉ፡፡

ለ.  የተቀባዉ ክፍል ሩብ ነዉ፡፡

ሐ. 

የተቀባዉ ክፍል ሁለት ሩብ ወይም ግማሽ ነዉ፡፡

መ. ከዚህ በታች የተቀባዉ ክፍል ከ 0 እስከ 4 ላለዉ ክፍል ምን ይባላል?




**መፍትሔ፡-** ሩብ ይባላል፡፡

## መልመጃ 4.2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።
   ሀ. አንድ ሙሉ ስንት ሩብ ይሆናል?
   ለ. አንድ ግማሽ ዳቦ ስንት ሩብ ይሆናል?
   ሐ. ስንት ግማሾች አንድ ሙሉ ይሆናሉ?
   መ. ግማሽን ለሩቦች መክፈል ይቻላል?
2. ታደለች የአንድ ቅርጽ ግማሹን ጥቁር፤ ሩቡን ግራጫ እና ሩቡን ነጭ እንዲሆን ትፈልጋለች። ስለዚህ ታደለች የምትፈልገዉ ቅርጽ ከሚከተሉት የትኛዉን ይመስላል?




3. ከዚህ በታች ያሉትን ምስሎች በማየት የተቀባዉን ክፍል በትክክል መልሱ።



ሀ የተቀባዉ ክፍል ________ ነዉ።



ለ. የተቀባዉ ክፍል __________ ነዉ።

4. ከዚህ በታች ያለዉ የብርቱካን ክፍል ምን ያህል እንደሆነ በተሰጠዉ ቦታ ሙሉ፡፡

ሀ.  የብርቱካን____________ ነዉ

ለ.  የብርቱካን____________ ነዉ

ሐ.  የብርቱካን____________ ነዉ

5. የ 44 ሎሚዎች ሩብ ስንት ነዉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

አንድን ሙሉ ነገር እኩል ቦታ ስንከፍለዉ የሚናገኛቸዉ ሁለት ክፍሎች እያንዳንዱ ግማሽ ይባላል፡፡ አንድን ሙሉ ነገር አራት ቦታ እኩል ስንከፍለዉ የሚናገኛቸዉ አራት ክፍሎች እያንዳንዱ ክፍል ሩብ ይባላል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡
   ሀ. አንድ ሙሉ ለሁለት እኩል ሲከፈል እያንዳንዱ ክፍል ግማሽ ይባላል፡፡
   ለ. አንድ ግማሽ ለሁለት እኩል ሲከፈል እያንዳንዱ ክፍል ሩብ ይባላል፡፡
   ሐ. አራት ግማሾች አንድ ሙሉ ይሆናሉ፡፡
2. በሚከተለዉ ምስል የተቀባዉን ክፍል ሩብ ወይም ግማሽ በማለት በባዶ ቦታ ጻፉ፡፡

ሀ.  የተቀባዉ ክፍል ________________ ነዉ፡፡

ለ.  የተቀባዉ ክፍል ________________ ነዉ፡፡

3. አንድ ሙሉ ነጭ ዉረቀት አዉጡና ጫፍና ጫፉን በማገናኘት እኩል እጠፉት፡፡ አንዱ የታጠፈዉ ወረቀት የሙሉ ወረቀት ምን ያህል ይሆናል?
4. አንድ ቦታ የታጠፈን ወረቀት በድጋሚ እኩል እጠፉት፡፡ እጥፋቶችን በመዘርጋት የታጠፈበትን ቦታ በእርሳስ

አስምሩ፡፡ በእርሳስ ባሰመራችሁበት ቦታ ቁረጡ፡፡ ወረቀቱ ስንት ቦታ ተከፈለ? ቆርጣችሁ ያወጣችሁት ወረቀት የሙሉ ወረቀት ምን ያህል ነዉ?

5. የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

ሀ.  የተቀባዉ ጥቁሩ ቀለም የጠቅላላዉ ____________ነዉ ፡፡

ለ.  ቀዩ እና ጥቁሩ በአንድነት የጠቅላላዉ ____________ ናቸዉ፡

6. ሁለት ግማሾች እኩል የሚሆኑት ከ_______ ጋር ነዉ?

ሀ. ከአራት ሩቦች ለ. ከሦስት ሩቦች

ሐ. ከአንድ ሙሉ ጋር መ. ሀ እና መ መልስ ናቸዉ

7. የሚከተሉትን ምሥሎች ግማሽ በመክፈል ግማሹን ቀቡ፡፡




8. በሚከተሉት ምሥሎች የተቀቡት ክፍሎች ግማሽ ወይም ሩብ በማለት በባዶ ቦታዎች ጻፉ፡፡

# ምዕራፍ 5

## ሥርዓተ- ጥለት (ፓቴርን)

**መግቢያ፡** በዚህ ምዕራፍ ሥርዓተ-ጥለት ምን እንደሆነ ለማስረዳት የተለያዩ ሥዕሎች፣ የቁጥር መስመሮች እና ቁጥሮች በምሳሌ እና በመልመጃ ዉስጥ ተካትተዋል፡፡ ስለዚህ ማስታወሻዎችን ማንበብ እና ጥያቄዎችን ደጋግሞ መሥራት ዕዉቀት ለማግኘት ይረዳል፡፡

**የትምህርቱ ዓላማ፡-**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የድግግሞሽ ሥርዓተ-ጥለቶችን ትረዳላችሁ፡፡

## 5.1. የድግግሞሽ ሥርዓተ-ጥለት ምድብ

**መግቢያ፡-** በዚህ ንዑስ ርዕስ የሚደጋገሙ ሥርዓተ-ጥለቶችን በቁጥሮች ፣ በሥዕሎች እና በተለያየ መልኩ ስለቀረቡ በተግባር እና በምሳሌ የቀረቡ ጥያቄዎችን በመረዳት ሥሩ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የድግግሞሽ የሥርዓተ-ጥለት ምድቦችን ትለያላችሁ፡፡

**ተግባር 5.1**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. ቁጥሮችን ከ 2 በመጀመር ሁለት ሁለት እየዘለላችሁ እስከ 50 ድረስ ቁጠሯቸዉ፡፡

ለ. በቁጥር መስመር ላይ ቁጥሮችን ሦስት ሦስት በመዝለል መቁጠር ትችላላችሁ? መቁጠር ከቻላችሁ፡-

- ከ1 በመጀመር ሦስት ሦስት እየዘለላችሁ ቁጠሩ።
- ከ 3 በመጀመር ሦስት ሦስት እየዘለላችሁ ቁጠሩ።

**ማስታወሻ፡-** *ሥርዓተ-ጥለት ማለት ሥርዓት ባለዉ መንገድ ዕቃዎችን፣ ቁጥሮችን፣ ሥዕሎችን እና የመሳሰሉትን መደርደር ወይም ማስቀመጥ ማለት ነዉ። የሚደጋገም ሥርዓተ ጥለት ማለት ዋና ነገር የሚደጋገም አጭሩ ምድብ ነው።*

ምሳሌ፡ 1. የሚከተሉትን ሥርዓተ-ጥለቶች በመመልከት ቀጥሎ ያሉ ተርሞችን(አባላትን) በጎደለዉ ቦታ ሙሉ፤ ዋናዉን ፈልጉ።

ሀ. □ ○ △ □ ○ △ ___ ___ ___ , ___ ____ ____

ለ. 200፣ 100 ፣ 10፣ 200፣ 100፣ 10፣___ ___ ____ ,

ሐ.  ____ ____ ____

**መፍትሔ**

ሀ. □ ○ △ □ ○ △ ዋናዉ □ ○ △ ነዉ።

ለ.200፣ 100 ፣ 10, 200፣ 100 ፣ 10, 200፣ 100 ፣ 10

ዋናዉ 200፣ 100 ፣ 10 ነዉ።

ሐ. , , 

ዋናዉ  ነዉ።

**መልመጃ 5.1**

1. በሚከተለዉ የቁጥር መስመር ላይ ያለዉን ሥርዓተ-ጥለት በመመልከት የጎደሉትን ቦታዎች ሙሉ።




2. ከላይ በተሰጠዉ ሥርዓተ-ጥለት ላይ ሁለተኛዉ ተርም 10 ሲሆን

   ሀ. አራተኛዉ ተርም ማን ነዉ?

   ለ. ስድስተኛ ተርም ማን ነዉ?

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመልከት ከሥርዓተ-ጥለቱ የጎደሉ ተርሞችን(አባላትን) በባዶ ቦታዎች ላይ ሙሉ።

ሀ. 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ ____፣ ____፣ ____፣_____፣ ____፣_____

ለ. 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ ____፣ ____፣ ____፣_____፣ ____፣_____

ሐ. 0፣ 8፣ 16፣ 24፣ ____፣ ____፣ ____፣_____፣ ____፣__

መ.  __ __ __፣___ __ __

ሠ. 500፣10፣50፣ 500፣10፣50___፣ ___፣ ___

ረ.  ,___ ___ ___

ሰ.  , ___ ___ ___ ___

## 5.2. የጎደሉ የሥርዓተ-ጥለት አባላት

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ የጎደሉ ተርሞች ወይም ቁጥሮች ቅደም ተከተላቸዉን ተጠብቆ እንዴት እንደሚሟሉ የተሰጡትን ምሳሌዎች በመረዳት መልመጃዎችን መሥራት ትችላላችሁ።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በሥርዓተ-ጥለት የጎደሉ ተርሞችን ታሟላላችሁ፡፡
- የሚደጋገሙ ሥርዓተ ጥለቶችን በማርዘም ቀጣይ አባላትን ትገምታላችሁ፡፡

**ተግባር፡5.2**

1. የሚከተለዉ ሥዕል በመመልከት ከ ሀ እስከ መ ያሉትን ጥየቀዎች ሥሩ፡፡




ሀ. ከላይ በተሰጠዉ ሥርዓተ ጥለት ላይ ከ 30 ቀጥሎ ያለዉ ተርም ማን ነዉ?

ለ. በእያንዳንዱ ተርም መካከል ያለዉ ምድብ ስንት ነዉ?

ሐ. በሥርዓተ ጥለቱ የጎደሉ ተርሞችን ሙሉአቸዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ምድብ ማለት በአንድ ሥርዓተ-ጥለት ዉስጥ በተርሞች መካከል የሚገኝ ልዩነት ሲሆን የሚቀጥሉ ተርሞችን ለማግኘት እንጠቀማለን፡፡

**ምሳሌ**

ሀ. በ 3፣ 6፣ 9፣ 12፣ 15፣ 18፣ 21፣ 24 ሥርዓተ-ጥለት በእያንዳንዱ ተርም መካከል ያለዉ ልዩነት 3 በመሆኑ ምድቡ 3 ነዉ፡፡ ይህ አዳጊ ሥርዓተ ጥለት ነዉ፡፡

ለ. በ 345 345 345 345 345 _ _ _ ይህ ሥርዓተ ጥለት የሚደጋገም ሥርዓተ ጥለት ነዉ፡፡ ዋናዉ ወይም ምድቡ 345 ነዉ፡፡

**መልመጃ 5.2**

1. በሚከተለዉ የቁጥር መስመር ላይ የጎደሉ ቁጥሮችን በመሙላት ከታች ያሉ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ሀ. ከ 20 ቀጥሎ በስተቀኝ ያለዉ ተርም ስንት ነዉ?

ለ. አንደኛዉ ተርም 0 ነዉ፡፡ ሰባተኛዉ ተርም ስንት ነዉ?

ሐ. በየተርሞች መካከል ያለዉ ምድብ ስንት ነዉ?

መ. ከላይ የተሰጠዉን የቁጥር መስመር በማየት 5ኛ , 6ኛ ,8ኛ እና 9ኛ ተርሞች እነማን ናቸዉ?

2. የሚከተሉትን ሥርዓተ-ጥለቶች በመመልከት ቀጥሎ ያሉትን ተርሞች ሙሉ።

ሀ.  ____ ___ ___ ___

የሥርዓተ-ጥለት ምድብ ________ ነዉ።

ለ. 🕯🔔✡🕯🔔✡🕯🔔✡___ ___ ___ ___ ___ _____________

የሥርዓተ-ጥለት ምድብ ________ ነዉ።

ሐ. 5፣ ___፣ 15፣ ___፣ ___፣ 30፣ ___፣ ___፣ 45፣ ___

የሥርዓተ-ጥለት ምድብ ________ ነዉ።

መ. 2፣ 4፣ __፣ 8፣___፣___፣ ___፣ 16፣ 18፣ ___ የዚህ የሥርዓተ-ጥለት ምድብ ___ ነዉ

3. በሚከተሉት የሚደጋግሙ እና አዳጊ ሥርዓተ-ጥለቶች ዉስጥ የጎደለዉን ተርም ሙሉ።

ሀ. 606 606 606 606 606 ____ ____ ____ ____

ለ. 4442 4442 4442 4442 ____ ____ ____ ____

ሐ. 10፣ 20፣_____፣_____፣ 50፣_____፣_____፣_____

መ. 7፣ ______፣______፣______፣______፣ 42፤ ______

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

ሥርዓተ ጥለት (ፓቴርን) ማለት ቁጥሮችን፤ ዕቃዎችን ወይም የተለያዩ ነገሮችን ሥርዓት ባለዉ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መደርደር ሲሆን በእያንዳንዱ አባል(ተርም) መካከል ያለዉ ልዩነት ምድብ ይባላል፡፡ በአንድ ሥርዓተ ጥለት ያለዉ ምድብ ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት መሆን አለበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. 6፣12 ፣18 ፣ 24፣30፣36፣42 የዚህ ሥርዓተ-ጥለት ምድብ 3 ነዉ፡፡

ለ. 3፣ 6፣ 9፣ 12፣ 15 ፣18 ፣ 24፣27፣30፣33፣36 የዚህ ሥርዓተ-ጥለት ምድብ 6 ነዉ፡፡

ሐ. ምድብ ማለት በሥርዓተ-ጥለት ዉስጥ በተርሞች መካከል ያለዉ ልዩነት ነዉ፡፡

መ. 9፣ 18 ፣ 27 ፣36 ፣45 ፣54፣63፣72 የዚህ ሥርዓተ-ጥለት ምድብ 9 ነዉ።

2. የሚከተሉትን ሥርዓተ-ጥለቶች በማየት የጎደለዉን ሙሉ።

ሀ. ◷✧❖⚐፤ __ __ __ __ ፤◷✧❖⚐፤ __ __ __ __

ለ. ☼♡♡፣ __ ____ __☼♡♡ ፣____ ____ _____

ሐ.  _____ _____ _____

መ. 10፣ 50 ፣50፣50፣__፣__፣__፣__፣10፣__፣__፣____፣____

3. ከዚህ በታች በቀረበዉ ሥርዓተ ጥለት ዉስጥ የጎደሉትን በመሙላት ቀጥሎ ከ ሀ እስከ መ ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ።




ሀ. ከ 40 ቀጥሎ ያለዉ ተርም ማን ነዉ?

ለ. ሰባተኛዉ ተርም ማን ነዉ?

ሐ. 110 የሥርዓተ-ጥለቱ ተርም ሊሆን ይችላል? እንዴት?

4. ከዚህ በታች ያሉ የእንቁላል ሥዕሎችን አቀማማጥ ሥርዓተ-ጥለት በመመልከት በባዶ ቦታዎች መቀመጥ ያለባቸዉን



የእንቁላሎች ብዛት የሚገልጹ ቁጥሮችን ሙሉ፡፡

____ ____፣____ _____

5. የሚከተለዉን የሥርዓተ-ጥለት አቀማመጥ በማየት ባዶ ቦታዎችን ሙሉ፡፡



# ምዕራፍ 6

## የርዝመት ፣ የክብደት እና የይዘት መለኪያዎች

**መግቢያ፡-** ርዝመት፣ ክብደት እና ይዘትን የምንለካበት የተለያዩ የመለኪያ ዓይነቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መለኪያዎች የተወሰኑት የመለኪያ አይነቶችን ብቻ በዚህ ምዕራፍ እናያለን፡፡ በተጨማሪ መለኪያዎች እንዴት እንደሚደመሩ እና እንደሚቀነሱ የተገለጸ ስለሆነ ምሳሌዎችን በሚገባ መሥራት የመልመጃ ጥያቄዎችን በቀላሉ ለመሥራት ያስችላል፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ርዝመትን፣ ክብደትን እና ይዘትን በባህላዊ የኢትዮጵያ መለኪያዎች እና በዘመናዊ መለኪያዎች ትለካላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ የርዝመት፣ የክብደት እና የይዘት መለኪያ ምድቦችን ትደምራላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ የርዝመት፣ የክብደት እና የይዘት መለኪያ ምድቦችን ትቀንሳላችሁ፡፡

## 6.1. ርዝመትን በባህላዊ፣በሜትር እና በሳንቲ ሜትር ምድቦች መለካት

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ከርዝመት መለኪያ ምድቦች ሜትር እና ሳንቲ ሜትር እንዴት እንደምንጠቀም እና መለኪያዎች ተመሳሳይ ስሆኑ መደመር እና መቀነስ እንደሚቻል ተገልጿል።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ከርዝመት መለኪያ ምድቦች ዉስጥ ሁለቱን (ሳ.ሜ እና ሜ.) ትለያላችሁ።
- ዘመናዊ እና ባህላዊ የሆኑ የርዝመት መለኪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ ርዝመት ያላቸዉን ነገሮች ትለካላችሁ።

**ተግባር 6.1**

1. ርዝመት እንዴት ይለካል?
2. ሜትር ማለት ምን ማለት ነዉ? የርዝመት መለኪያ ምድብ ነዉ? ወይስ የርዝመት መለኪያ መሣሪያ ነዉ?

3. በክፍላችሁ ዉስጥ ያለዉን የሰሌዳ ርዝመት በክንዳችሁ እና በሜትር ለክታችሁ ተናገሩ፡፡

4. ከክፍላችሁ ረዥሙ ተማሪ ቁመቱ ምን ያህል ነዉ?

ማስታወሻ፡

- ሜትር እና ሳንቲ ሜትር መካከለኛ እና አጫጭር ርዝመቶችን ለመለካት የምንጠቀምባቸዉ የርዝሜት መለኪያ ምድቦች ናቸዉ፡፡
- ሜትር በአጭሩ ሲጻፍ ሜ. ሲሆን ሳንቲ ሜትር በአጭሩ ሲጻፍ ሳ.ሜ. ተብሎ ይጻፋል፡፡

ከዚህ በታች የሚታዩአቸዉ ባህላዊ እና ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ መሣሪያዎች ናቸዉ፡፡






ምሳሌ

1. የደብተራችሁ ረዥሙ የጎን ጠርዝ ርዝመት ምን ያህል ነዉ?

መፍትሔ፡ መምህሩ እንዴት እንደምትለኩ ያሳያችኋል፡፡

2. ሜትር እና ሳንቲ ሜትር ልዩነታቸዉ ምንድ ነዉ?

መፍትሔ፡ 1 ሜትር 100 ሳንቲ ሜትር ነዉ፡፡

3. ሜትር በመጠቀም ምን መለካት ይቻላል? ሳንቲ ሜትር በመጠቀም ምን መለካት ይቻላል?

መፍትሔ፡ መጠነኛ ርዝመቶችን በሜትር እንለካለን፡፡ ለምሳሌ፡ ሰሌዳ፣ የቤቶች ርዝመት፣ የኳስ ሜዳ ርዝመት ወዘተ. እንድሁም አነስተኛ ርዝመቶችን በሳንቲ ሜትር መለካት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- የደብተር ፣ እርሳስ፣ እስክርብቶ ወዘተ. መለካት ይቻላል፡፡

## መልመጃ 6.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ።

   ሀ. የመማሪያ ክፍላችሁ የሁለት ተጓዳኝ ጎኖች ርዝመት እኩል ነዉ?

   ለ.የመማሪያ ክፍላችሁ ረዥሙ ጎን ርዝመት በሜትር ስንት ነዉ? በሳንቲ ሜትር ስንት ነዉ?

   ሐ. የጥቁር ሰሌዳ ርዝመት በሜትር ምን ያህል ነዉ? ወደ ሳንቲ ሜትር ስትለዉጡ ስንት ይሆናል?

   መ. የመማሪያ ክፍላችሁ መዝጊያ ቁመት በሜትር ስንት ነዉ?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።

   ሀ. ሳንቲ ሜትር በጣም ትልቅ የሆኑ ርዝመቶችን ለመለካት እንጠቀማለን።

   ለ. ሜትር ከሳንቲ ሜትር ትልቅ የመለኪያ ምድብ ነዉ።

   ሐ. ደብተራችንን ለመለካት ከሜትር ይልቅ ሳንቲ ሜትር መጠቀም ይሻላል።

## 6.2. ተመሳሳይነት ያላቸዉን የርዝመት ምድብ መለኪያዎችን መደመር እና መቀነስ

መግቢያ፡ በዚህ ርዕስ ከላይ የተሰጡ የርዝመት መጠን መለኪያ ምድቦች ማለትም ሜትር እና ሳንቲ ሜትር እንዴት እንደሚደመሩ እና እንደሚቀነሱ በማስታወሻ እና በምሳሌዎች ስለተገለጹ አሰራሩን በመረዳት መልመጃዎች መስራት ይቻላል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የርዝመት መጠን መለኪያ ምድቦች ትደምራላችሁ፡፡
- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የርዝመት መጠን መለኪያ ምድቦች ትቀንሳላችሁ፡፡

ተግባር 6.2

1. የመማሪያ ክፍላችሁን ሁለት ተጓዳኝ ጎኖች ርዝመት በመለካት አንድ ላይ ስንት እንደሆኑ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

2. አንድን ነገር በሜትር እና በሳንቲ ሜትር ከለካን በኋላ እንዴት መደመር ወይም መቀነስ እንችላለን? ተወያዩ፤ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩት።

ማስታወሻ:

- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የርዝመት መጠኖችን መደመር ወይም መቀነስ የምንችለዉ ተመሳሳይ ምድብ ሲኖራቸዉ ነዉ።

ለምሳሌ: ሜትር ከሜትር ጋር ፤ ሳንቲ ሜትር ከሳንቲ ሜትር ጋር ይደመራል፤ ይቀነሳል።

ምሳሌ1. ሀ. 20 ሳንቲ ሜትር ሽቦ እና 70 ሳንቲ ሜትር ሽቦ አንድ ላይ ስንት ነዉ?

መፍትሔ: 20 ሳ.ሜ + 70 ሳ.ሜ = 90 ሳ.ሜ ይሆናል።

ለ. ታረቀኝ የ 2ኛ ክፍል ተማሪ ነዉ። ከቤቱ እስከ ትምህርት ቤት ያለዉ ርቀት 200 ሜትር ነዉ። ታረቀኝ ከቤቱ እስከ ትምህርት ቤት ደርሶ መልስ ምን ያህል ይጓዛል?

**መፍትሔ**፡- ታረቀኝ ከቤቱ እስከ ትምህርት ቤት ያለዉ ርቀት 200 ሜትር ነዉ፡፡ ከትምህርት ቤት እስከ ቤቱ ያለዉ ርቀት 200 ሜትር ነዉ፡፡ ደርሶ መልስ ርቀት 200 ሜትር + 200 ሜትር = 400 ሜትር ይሆናል፡፡

ምሳሌ 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመደመር እና በመቀነስ አስሉ፡፡

ሀ. 10 ሜ + 10 ሜ =____________________

ለ. 85 ሜ + 5 ሜ =____________________

ሐ. 10 ሳ.ሜ - 2 ሳ.ሜ =____________________

መ. 60 ሳ.ሜ - 10 ሳ.ሜ =____________________

**መፍትሔ**፡ 2 ሀ. 20 ሜ     ለ. 90 ሜ

ሐ. 8 ሳ.ሜ     መ. 50 ሳ.ሜ

**መልመጃ 6.2**

1. የሚከተሉትን የርዝመት መለኪያዎች ደምሩ፡፡

ሀ. 11ሜ+3ሜ =_______ ለ. 40ሜ + 10 ሜ =______

ሐ. 100 ሜ+300 ሜ =_____ መ. 80 ሜ + 11ሜ =______

ሠ. 60ሳ.ሜ + 20 ሳ.ሜ =__ ረ. 25 ሳ.ሜ + 25 ሳ.ሜ =__

**2.የሚከተሉትን የርዝመት መለኪያዎች ቀንሱ።**

ሀ. 10ሜ - 3ሜ =____ ለ. 15 ሜ - 9 ሜ =____

ሐ. 30 ሜ - 3 ሜ =____ መ. 42 ሳ.ሜ - 3 ሳ.ሜ =___

ሠ. 65 ሳ.ሜ - 5 ሳ.ሜ=____ ረ. 95 ሳ.ሜ - 10 ሳ.ሜ =___

3.የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብለሞች ሥሩ።

ሀ. አስቴር የ 2ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ከመኖሪያ ቤታቸዉ እስከ አክስቷ ቤት ያለዉ ርቀት 350 ሜትር ነዉ። አስቴር ከቤታቸዉ እስከ አክስቷ ቤት ደርሶ መልስ ስንት ሜትር ትጓዛለች?

ለ. የአንድ እርሳስ ርዝመት 8 ሳንቲ ሜትር ነዉ። እርሳሱ ሲቀረጽ 3 ሳንቲ ሜትር ከቀነሰ አሁን የሚቀረዉ የእርሳሱ ርዝመት ምን ያህል ነዉ?

## 6.3. ክብደትን በግራም እና በኪሎግራም ምድቦች መለካት

**መግቢያ፡-** ክብደት ምን እንደሆነ እና ክብደት እንዴት እንደሚለካ፤ እንድሁም በዚህ ምዕራፍ የተሰጡ የክብደት መለኪያ ምድቦች ምን እንደሆኑ በመጽሐፉ በሥዕል እና በጽሑፍ ተካትቷል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ክብደትን በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪያ፣ በግራም እና በኪሎ ግራም ትለካላችሁ፡፡

**ተግባር፡ 6.3**

1. ተማሪዎች ክብደታችሁን እንዴት ታዉቁታላችሁ?
2. ክብደታችሁ ምን ያህል እንደሆነ ተለክታችሁ በሚቀጥለዉ ቀን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. በክፍላችሁ በክብደት የሚበልጠዉ ተማሪ ማን ነዉ? የሚያንሰዉ ተማሪ ማን ነዉ?
4. የኪሎ ግራምን እና የግራም ልዩነት ምንድ ነዉ?

5. የክብደት መለኪያ መሣሪያ ምን ይባላል?

6. የክብደት መለኪያ መሣሪያዎችን የት ቦታ ነዉ ያያችሁት?

**ማስታወሻ፡**

- ዕቃዎች ወይም የተለያዩ ነገሮች ምን ያህል እንደሚከብዱ ለማወቅ የተለያዩ የክብደት መለኪያዎችን እንጠቀማለን፡፡
- ክብደትን ለመለካት የምንጠቀምበት መሣሪያ ሚዛን ሲሆን ግራም እና ኪሎ ግራም የክብደት መለኪያ ምድቦች ናቸዉ፡፡
- ኪሎግራም በአጭሩ ሲጻፍ ኪ.ግ ሲሆን ግራም በአጭሩ ሲጻፍ ግ ተብሎ ይጻፋል፡፡

ከዚህ በታች ያሉ የክብደት **መለኪያ መሣሪያዎች** ወይም ሚዛኖች ናቸዉ፡፡



ምሳሌ፡- 1. የክብደት መጠን **መለኪያ ምድቦች** እነማን ናቸዉ?

**መፍትሔ፡** ኪሎግራም ፧ ግራም

2 ስኳር የሚሸጠዉ በምን አይነት የክብደት **መለኪያ ምድቦች** ነዉ?

**መፍትሔ፡** ግራም ወይም ኪሎግራም

3. የክብደት **መለኪያ መሣሪያ** ምን ይባላል?

*መፍትሔ፡* ሚዛን

## መልመጃ 6.3

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት መልሱ፡፡

ሀ. ወደ ገበያ ወይም ወደ ሱቅ ሄዳችሁ ጨዉ ወይም ስኳር ስትገዙ በምን አይነት መለኪያ ነዉ የምትገዙት?

ለ. የተለያዩ የሚዛን አይነቶችን ታዉቃላችሁ? በሥዕል መግለጽ ትችላላችሁ?

ሐ. ከዚህ በታች ካሉ ምሥሎች የክብደት መለኪያ መሣሪያ የሆኑት የትኞች ናቸዉ?




## 6.4. ተመሳሳይነት ያላቸዉን የክብደት ምድብ መለኪያዎችን መደመርና መቀነስ

**መግቢያ፡-** የክብደት መለኪያዎች መደመር ወይም መቀነስ የሚቻለዉ መለኪያዎች አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ምድብ ሲኖራቸዉ ብቻ ነዉ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የክብደት ምድብ መለኪያዎች ትደምራላችሁ፡፡
- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የክብደት ምድብ መለኪያዎች ትቀንሳላችሁ፡፡

## ተግባር 6.4

1. ለብቻችሁ ሚዛን ላይ ወጥታችሁ እና ዕቃ ተሸክማችሁ ሚዛን ላይ ስትመዘኑ እኩል ይሆናል? ለምን?
2. ምን አይነት የክብደት መለኪያ ተጠቀማችሁ?
3. በክፍላችሁ ከሚገኙ ተማሪዎች ክብደቱ አነስተኛ የሆነ ተማሪ ማን ነዉ? ምን ያህል ነዉ?
4. በክፍላችሁ ከሚገኙ ተማሪዎች ክብደቱ ትልቅ የሆነ ተማሪ ማን ነዉ? ምን ያህል ነዉ?
5. ቸርነት ከገበያ 3 ኪሎ ግራም ምሥር፤2 ኪሎ ግራም ስኳር እና 6 ኪሎ ግራም አተር ቢገዛ ቸርነት በጠቅላላዉ የገዛዉ ስንት ኪሎ ግራም ነዉ?
6. ገበያነሽ 500 ግራም ቅመማቅመም ገዝታ 300 ግራም ቢትጠቀም ስንት ግራም ይቀራታል?

ማስታወሻ፡ 1. ክብደትን መደመር ሆነ መቀነስ የሚቻለዉ ምድባቸዉ ተመሳሳይ ሲሆን ነዉ፡፡

2. ክብደትን ለመለካት ኪሎግራም ወይም ግራም መጠቀም ይቻላል፡፡

3. አንድ ኪ.ግ 1000 ግ ነዉ፡፡

ምሳሌ፡ 1. አቶ መሀመድ 50 ኪሎ ግራም በቆሎ ከወይዘሮ ኡፋይሰ ገዛ፡፡ በተጨማሪ 25 ኪሎ ግራም በቆሎ ከአቶ ተስፋዬ ገዛ፡፡ አቶ መሀመድ በጠቅላላ የገዛዉ በቆሎ ምን ያህል ነዉ?

መፍትሔ፡ 50 ኪሎ ግራም + 25 ኪሎ ግራም = 75 ኪሎ ግራም

2 . ወ/ሮ ለምለም የእህል መጋዘን አላት፡፡ በመጋዘኗ ዉስጥ 900 ኪሎ ግራም ጤፍ አላት፡፡ በመጋዘን ከነበረዉ ጤፍ ዉስጥ ለደንበኞቿ 765 ኪ.ግ ሸጣለች፡፡ በመጋዘኗ ዉስጥ የቀረዉ የጤፍ መጠን ምን ያህል ነዉ?

መፍትሔ፡ 900 ኪ. ግ. - 765 ኪ. ግ. = 135 ኪ.ግ

ምሳሌ 3. የሚከተሉትን የክብደቶች አስሉ፡፡

ሀ. 11 ኪ.ግ + 21 ኪ.ግ =_______

መፍትሔ፡ 32 ኪ. ግ

ለ. 81 ኪ.ግ -13 ኪ.ግ =________

መፍትሔ፡ 68 ኪ. ግ

## መልመጃ 6.4

1. የሚከተሉትን ክብደቶች አስሉ፡፡

ሀ. 67 ኪ.ግ+17 ኪ.ግ =____ ለ. 83 ኪ.ግ+19 ኪ.ግ =___

ሐ. 13 ኪ.ግ+11 ኪ.ግ =____ መ. 55 ኪ.ግ+10 ኪ.ግ =___

ሠ. 47 ኪ.ግ+12 ኪ.ግ =____ ረ. 92 ኪ.ግ - 11 ኪ.ግ =_

ሰ. 73 ኪ.ግ - 9 ኪ.ግ =___ ሸ. 10 ግ - 3 ግ =___

ቀ. 97 ግ + 15 ግ =___

2. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ፡፡

ሀ. ከአቶ ሰማያት የወርቅ መሸጫ ሱቅ ሁለት እህትማማቾች 4 ግራምና 5 ግራም ወርቅ ገዙ፡፡ ሁለቱ እህትማማቾች የገዙት ወርቅ አንድ ላይ ስንት ግራም ነዉ?

ለ. ወ/ሮ ሰላምነሽ ክብደታቸዉ 97 ኪ.ግ ነዉ ፡፡ የወ/ሮ ሰላምነሽ ክብደት መጨመር ለጤንነታቸዉ ጥሩ ባለመሆኑ እስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ከ 3 ወር በኋላ 25 ኪ.ግ

ቀነሱ፡፡ አሁን ወ/ሮ ሰላምነሽ ያላቸዉ ክብደት ምን ያህል ነዉ?

## 6.5. ይዘትን በሊትርና ሚሊ ሊትር ምድቦች መለካት

**መግቢያ፡-** ይዘት በተለይም ፈሳሽ የሆኑ ነገሮች እንዴት እንደሚለኩ እና የተወሰኑ የይዘት መለኪያ ምድቦች እና መሣሪያዎች ምን እንደሆኑ በዚህ ንዑስ ርዕስ ትማራላችሁ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ይዘትን በኢትዮጵያ ባህላዊ መለኪያ፣ በሊትር እና ሚሊ ሊትር ትለካላችሁ፡፡

**ተግባር 6.5**

1. ፈሳሽ የሆኑ ነገሮች በምን እንደሚለኩ ተናገሩ፡፡
2. ወተት እና ዘይት በምን ይለካል?
3. ሞተረኞች በየመንገዱ ቤንዚን ሲያልቅባቸዉ የሚገዙት በምን ዓይነት መስፈሪያ ነዉ?

ማስታወሻ፡

- ፈሳሽ የሆኑ ነገሮችን በተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ መለኪያዎች መለካት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ጣሳ፣ እንስራ፣ ቅል ወዘተ ባህላዊ መለኪያ ሲሆኑ ዘመናዊ ከሆኑ የይዘት መለኪያ ምድቦች ዉሰጥ ጥቂቶች ሊትርና ሚሊ ሊትር ናቸዉ፡፡
- ሊትር በአጭሩ ሲጻፍ ሊ. ሲሆን ሚሊ ሊትር በአጭሩ ሲጻፍ ሚ.ሊ. ተብሎ ይጻፋል፡፡
- አንድ ሊትር 1000 ሚሊ ሊትር ነዉ፡፡

## የይዘት መለኪያ መሣሪያዎች










ምሳሌ፡ 1. የይዘት መለኪያ ምድቦች እነማን ናቸዉ?

መፍትሔ፡- ሊትር እና ሚሊ ሊትር

2 ዘይት፤ ቤንዚን እና የመሳሰሉ ፈሳሽ ነገሮች በምን ይለካሉ? **መፍትሔ:** በሊትር

## **መልመጃ 6.5**

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

   ሀ. በአካባቢያችሁ ወተት በምን ይሸጣል?

   ለ. የአንድን ፈሳሽ ነገር ይዘት ለመለካት ምን አይነት የመለኪያ ምድብ እንጠቀማለን?

   ሐ. ሊትር እና ሚሊ ሊትር ምን አይነት ግንኙነት አላቸዉ?

   መ. ከዚህ በታች ያሉ ምሥሎችን በማየት የፈሳሽ ነገር መለኪያ መሣሪያዎችን ለዩ።



## 6.6. ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት ምድብ ያላቸዉ የይዘት መጠን መለኪያዎችን መደመር እና መቀነስ

መግቢያ፡ ከዚህ በፊት ይዘትን የተለያዩ የአካባቢ ዕቃዎችን እና መደበኛ የመለኪያ ምድቦች በመጠቀም መለካት እንደምንችል አይተናል፡፡ አሁን በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ሊትር እና ሚሊ ሊትር የይዘት መለኪያ ምድቦችን አንድ አይነት በማድረግ መደመር እና መቀነስን ትማራላችሁ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የይዘት ምድቦች ትደምራላችሁ፡፡
- ተመሳሳይነት ያላቸዉን የይዘት ምድቦች ትቀንሳላችሁ፡፡

**ተግባር 6.6**

1. በአካባቢያችሁ በሚገኙ ሱቆች የሚሸጡ ዘይቶች ባለስንት ሊትር ናቸዉ?

2. ወ/ሮ ተዋበች 2 ሊትር ዘይት ገዝታ ስላለቀባት በተጨማሪ 4 ሊትር ዘይት ገዛች፡፡ ወ/ሮ ተዋበች በጠቅላላ ስንት ሊትር ዘይት ገዝታለች?

3. በለጠች 20 ሊትር ዉሃ ገዛች፡፡ ከገዛችዉ ዉሃ 8 ሊትር ለመጠጥ ከተጠቀመች የሚቀራት ምን ያህል ሊትር ዉሃ ነዉ?

ማስታወሻ

- ሊትር እና ሚ. ሊ የፈሳሽ ነገሮች መለኪያ ምድቦች ሲሆኑ የፈሳሽ ነገር መለኪያ መሣሪያዎች የተለያዩ ናቸዉ፡፡
- ሊትር በአጭሩ ሲጻፍ ሊ እና ሚሊ ሊትር በአጭሩ ሲጻፍ ሚ.ሊ ተብሎ ይጻፋል፡፡

ምሳሌ፡-

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመደመር ወይም በመቀነስ አስሉ

ሀ. 2 ሊ+29 ሊ =_____ ለ. 19 ሊ+20 ሊ =_____

ሐ. 5 ሚ.ሊ+95 ሚ.ሊ =__ መ. 82 ሚ.ሊ-28 ሚ.ሊ =____

ሠ. 22 ሚ.ሊ-11 ሚ.ሊ =____ ረ. 52 ሊ - 7 ሊ =_____

**መፍትሔ፡** ሀ. 31 ሊ. ለ. 39 ሊ. ሐ. 100 ሚ.ሊ.

መ. 54 ሚ.ሊ.  ሠ. 11 ሚ.ሊ.  ረ. 45 ሊ.

## መልመጃ 6.6

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ።

ሀ. 15 ሊ + 13 ሊ =__________________

ለ. 9 ሊ + 32 ሊ =__________________

ሐ. 36 ሊ - 10 ሊ =__________________

መ. 98 ሚ.ሊ - 67 ሚ.ሊ =______________

ሠ. 100 ሚ. ሊ + 20 ሚ.ሊ =_________ሚሊ ሊትር

2. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ።

ሀ. ተዘራ እና ዮናስ አንድ ባሊዲ ዉሃ ለመሙላት ፈለጉ። ተዘራ 12 ሊትር ዉሃ በባሊዲ ዉስጥ ጨመረ። ዮናስ 8 ሊትር ዉሃ በባሊዲ ዉስጥ ሲጨምር ባሊዲዉ ሞላ። በአጠቃላይ በባሊዲ ዉስጥ የተጨመረዉ የዉሃ መጠን ምን ያህል ነዉ?

ለ. ወ/ሮ መዓዛ 39 ሊትር ዘይት በሱቅ ዉስጥ አላት። ከዚህ ዉስጥ ለወ/ሮ አየለች 5 ሊትር ዘይት ሸጠች። ያልተሸጠዉ ዘይት ምን ያህል ነዉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

ርዝመት፣ ክብደት እና ይዘትን ለመለካት ዘመናዊ እና ባህላዊ መለኪያዎች አሉ፡፡ ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ ምድቦች ሜትር እና ሚሊ ሜትር ሲሆኑ ባህላዊ መለኪያ ምድቦች ደግሞ ክንድ፣ ስንዝር፣ ገመድ፣ እግር እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ ዘመናዊ የክብደት መለኪያ ምድቦች ኪሎ ግራም እና ግራም ሲሆኑ ባህላዊ የክብደት መለኪያዎች የተለያዩ ባህላዊ ዕቃዎችን በመጠቀም ወይም በእጅ ክብደታቸዉን በመገመት ነዉ፡፡ ዘመናዊ የይዘት መለኪያ ምድቦች ሊትር እና ሚሊ ሊትር ሲሆኑ ባህላዊ የይዘት መለኪያዎች ደግሞ እንደ እንስራ፣ ቅል እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ነዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ፊደል ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ዉስጥ የክብደት መለኪያ ምድብ የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ኪሎ ግራም ለ. ሊትር ሐ.ሳንቲ ሜትር መ. ሜትር

2. ከሚከተሉት ዉስጥ የርዝሜት መለኪያ ምድብ የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ሳንቲ ሜትር ለ. ሜትር ሐ. ሊትር መ. ሀ እና ለ

3. ከሚከተሉት ዉስጥ የይዘት መለኪያ ምድብ የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሳንቲ ሜትር ለ. ሊትር

ሐ.ግራም መ. ሚሊ ግራም

4. ከሚከተሉት ዉስጥ የርዝመት መለኪያ መሣሪያ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ማስመሪያ ለ. ታፕ ሐ. ሚዛን መ.መልሰ የለም

5. ከዚህ በታች ያለዉን ሥዕል በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

1. እነኚህን መለኪያዎች አይታችሁ ታዉቃላችሁ?
2. የሚታዉቋቸዉን ስማቸዉን ጻፉ፡፡

3. የይዘት መሊኪያ የሆኑት የትኞች ናቸዉ?




6.የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. የርዝመት መለኪያ ማለት ምን ማለት ነዉ?

ለ. የርዝመት መለኪያ መሣሪያዎችን ጻፉ፡፡

ሐ. በክብደት መለኪያ ምድቦች እና በክብደት መለኪያ መሣሪያዎች መካከል ምን ልዩነት አለ?

መ. የይዘት መለኪያ ምድቦችን ጻፉ፡፡

ሠ. የይዘት መለኪያ ምድብ መሣሪያ እና በይዘት መለኪያ ምድብ  መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ?

7.የሚከተሉትን ደምሩ፡፡

ሀ. 75 ሜ + 23 ሜ =_____ ለ. 19 ሜ + 27 ሜ = ____

ሐ. 13 ሳ.ሜ + 5 ሳ.ሜ = __ መ. 40 ሳ.ሜ + 5 ሳ.ሜ = ___

ሠ. 60 ሊ + 25ሊ = ____ ረ. 53 ሊ + 20 ሊ = ____

ሰ. 90 ግ + 5 ግ = _____ ሸ. 12 ግ + 40 ግ = _____

ቀ. 70 ኪ.ግ + 20 ኪ.ግ = __ በ. 13 ኪ.ግ + 40 ኪ.ግ = ___

**8.የሚከተሉትን ቀንሱ፡፡**

ሀ. 43 ሳ.ሜ - 23 ሳ. ሜ = __ ለ.67 ሳ.ሜ-20 ሳ.ሜ =___

ሐ. 85 ሳ.ሜ-25 ሳ.ሜ = ___ መ. 40 ሳ.ሜ+5 ሳ.ሜ = ___

ሠ. 37 ግ-17 ግ = ____ ረ. 90 ግ-40 ግ = _____

ሰ. 17 ሊ-10 ሊ = ____ ሸ. 28 ሊ-20 ሊ = ____

**9. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ፡፡**

ሀ. አንድ ጀርካን 20 ሊትር ዉሃ መያዝ ይችላል፡፡ ተመሳሳይ መጠን ያላቸዉ ሦስት ጀርካኖች ቢኖሩ በጠቅላላ ስንት ሊትር ዉሃ መያዝ ይችላሉ?

ለ. አቶ ዮሴፍ 25 ኪሎ ግራም አተር እና 30 ኪሎ ግራም ባቄላ በአህያ ጭኖ ወደ ገበያ ወሰደ። አቶ ዮሴፍ በድምሩ ምን ያህል ኪሎ ግራም ጥራጥሬ ወደ ገበያ ወሰደ?

# ምዕራፍ 7

## የመረጃ አያያዝ

**መግቢያ፡-** በዚህ ምዕራፍ በአካባቢያችን የሚገኙ የተለያዩ መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ ፣ በአይነታቸዉ እንደሚለዩ እና እንደሚደራጁ በተለያየ መልኩ የተገለጸ ስለሆነ ይህንን ርዕስ በሚገባ ለመረዳት እና በተግባር መለማመድ ይጠበቃል፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡-**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ከአካባቢያችሁ መረጃ ትሰበስባላችሁ፡፡
- መረጃዎችን በመለየት በየአይነታቸዉ ትከፍላላችሁ፡፡
- የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሠንጠረዥ ታደራጃላችሁ፡፡
- በሠንጠረዥ የተደራጀዉን መረጃ ትተነትናላችሁ፡፡

## 7.1. መረጃ መሰብሰብ

**መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ የተለያዩ አነስተኛ መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ፣ እንደሚለዩ እና እንደሚደራጁ በተግባር እና በምሳሌዎች የተገለጸ ስለሆነ ይህንን መረዳት መልመጃዎችን ለመሥራት ይረዳል፡፡**

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ተማሪዎች ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በክፍላችሁ ዉስጥ፣ ከትምህርት ቤት ግቢ እና ከሰፈራቸዉ መረጃዎችን ትሰበስባላችሁ፡፡
- የተሰበሰበዉን መረጃ በየአይነታቸዉ ታደራጃላችሁ፡፡

**ተግባር 7.1**

1. በክፍላችሁ ዉስጥ ስንት ወንድ እና ስንት ሴት ተማሪዎች አሉ? ብዛታቸዉን ጻፉ፡፡
2. እያንዳንዳችሁ ስንት ወንድሞች እና እህቶች አሉአችሁ?

3. በቤታችሁ ወይም በጎረቤታችሁ ከብቶች አሉ? ካሉ በአንድ ቤት ያሉ የላሞች፣ የበሬዎች እና የጥጃዎች ብዛት መዝግባችሁ በክፍላችሁ ተናገሩ፡፡
4. በክፍላችሁ ዉስጥ ያሉ የወንበሮች እና የጠረጴዛዎች ብዛት ስንት ነዉ?

ማስታወሻ

1. መረጃ ለመሰብሰብ የሚሰበሰበዉን የመረጃ አይነት ማወቅ፤ የሚሰበሰብበትን ቦታ መለየት፣ መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት፡፡
2. መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በየዓይነታቸዉ ፣በመጠናቸዉ፣ በተሰሩበት የዕቃ አይነት በባህሪያቸዉ እና በመሳሰሉ መንገዶች ተደራጅተዉ መቀመጥ አለባቸዉ፡፡

ምሳሌ 1 . ከዚህ በታች ያሉ እንስሳትን የቤት እንስሳ እና የዱር እንስሳ በማለት ለዩአቸዉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ድመት | አንበሳ | ዉሻ | አህያ | ጅብ |
| በግ | ከርከሮ | በሬ | ድኩላ | ጦጣ |
| ነብር | በቅሎ | ፈረስ | ፍየል | የሜዳ አህያ |

| የቤት እንስሳ | የዱር እንስሳ |
|---|---|
| በግ | አንበሳ |
| በሬ | ነብር |
| አህያ | ጦጣ |
| በቅሎ | ጅብ |
| ድመት | ድኩላ |
| ፍየል | የሜዳ አህያ |
| ዉሻ | ከርከሮ |
| ፈረስ | |

2. ከዚህ በታች የተሰበሰቡ የፍራፍሬ እና የጥራጥሬ አይነቶችን በየአይነታቸዉ ለይታችሁ ጻፉ።

ባቄላ ሎሚ ብርቱካን ስንዴ ማንጎ በቆሎ

ጤፍ ፓፓያ ሽምብራ ማሽላ ሙዝ አናናስ

| ጥራጥሬ | ፍራፍሬ |
|---|---|
| ባቄላ | ማንጎ |
| ሽምብራ | ሎሚ |
| በቆሎ | ብርቱካን |
| ማሽላ | ሙዝ |
| ጤፍ | ፓፓያ |
| ስንዴ | አናናስ |

## መልመጃ 7.1

1. ከዚህ በታች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በየአይነታቸዉ ቀጥሎ ባለዉ ሠንጠረዥ ላይ ጻፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ብርቱካን | ዶሮ | መንደሪን | ፓፓያ | አቮካዶ |
| በግ | ስንዴ | ፍየል | ሙዝ | ሎሚ |
| በቅሎ | ባቄላ | ገብስ | አናናስ | አደንጓሬ |
| ማሽላ | ፈረስ | አህያ | በሬ | በቆሎ |
| ጤፍ | አተር | | | |

| የቤት እንስሳት | ጥራጥሬ | ፍራፍሬ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

2. ከዚህ በታች ያሉ የህንጻ መሣሪያዎች እና የመማሪያ ቁሳቁሶች በአንድ ሱቅ ዉስጥ ይገኛሉ። ቀጥሎ የተሰበሰቡትን መረጃዎች የህንጻ መሣሪያ እና የመማሪያ ቁሳቁስ በማለት ለሁለት ለዩአቸዉ።

እስክሪብቶ መዶሻ እርሳስ መጋዝ አካፋ

መጥረጊያ ሞረድ ደብተር ላጲስ ፍሽካ

ደወል ሜትር ብረትማዕዘን ማስመሪያ

| የህንጻ መሣሪያዎች | የመማሪያ ቁሳቁስ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

3. ከዚህ በታች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ፈሳሽ እና ጠጣር በማለት በሠንጠረዥ አደራጁ።

ዉሃ ወንበር ባትሪ ድንጋይ አልኮል

መዶሻ ወተት ሰሌዳ ነዳጅ

ዘይት ጠረጴዛ ለስላሳ ሞባይል ሳንታይዘር

| ፈሳሽ | ጠጣር |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የእንስሳት ዓይነቶችን እና የተክል አይነቶችን በመጻፍ በየአይነታቸዉ በመለየት በሠንጠረዥ ዉስጥ ጻፉ፡፡

| የእንስሳት አይነቶች | የተክል አይነቶች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## 7.2. ከሥዕላዊ ግራፍ መረጃዎችን በየአይነታቸዉ ማደራጀት

**መግቢያ፡-** ሥዕሎችን በመመልከት በአይነታቸዉ፣ በመጠናቸዉ፣በሚሰጡት አገልገሎት፣በሚኖሩበት ቦታ ወዘተ እንዴት መመደብ እና ማደራጀት እንደሚቻል በምሳሌዎች ስለተቀመጠ መልመጃዎችን በምሳሌዉ መሠረት መስራት

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ሥዕሎችን በመመልከት በሚሰጡት አገልግሎት፣ በየአይነታቸዉ እና የሚያመሳስላቸዉን ነገሮች በመለየት ትመድባላችሁ፡፡
- ሥዕሎችን በመመልከት በሚሰጡት አገልግሎት፣ በየአይነታቸዉ እና የሚያመሳስላቸዉን ነገሮች በመለየት ታደራጃላችሁ፡፡

## ተግባር 7.2

1. ከዚህ በታች ያሉትን እንስሳት የቤት እንስሳት እና በዱር (ጫካ) ዉስጥ የሚኖሩ በማለት ከታች በተሰጠዉ ሠንጠረዥ ጻፉአቸዉ፡፡




| የቤት እንስሳት | በዱር (ጫካ) ዉስጥ የሚኖሩ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

2. ከታች ያሉ ሥዕሎችን በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ሀ. በዉሃ ዉስጥ የሚኖሩ እንስሳት እነማን ናቸዉ?

ለ. በጫካ ዉስጥ የሚኖሩ እንስሳት እነማን ናቸዉ?

ሐ. በ ሀ እና ለ የተሰጡት ጥያቄዎችን መልስ ሠንጠረዥ በማዘጋጀት በሠንጠረዥ ዉስጥ ሙሉ፡፡

ምሳሌ፡

1. ከዚህ በታች ያሉ ሥዕሎች በመመልከት የህንፃ መሣሪያዎች እና የመማሪያ ቁሳቁስ በማለት በሠንጠረዥ አደራጁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
|  መቅረጫ |  መጋዝ |  አካፋ |  መዶሻ |
|  ሜትር |  መጽሐፍ |  የብረት ማዕዘን |  ዶማ |
|  ማስመሪያ |  ቆንጨራ |  ቦርሳ |  መሮ |
|  መሰላል |  ማጭድ |  ደብተር |  ላጲስ |
|  እርሳስ |  ውሃ ልክ |  እስክርብቶ |  ወረቀት |

**መፍትሔ፡**

| የህንፃ መሣሪያዎች | የመማሪያ ቁሳቁሶች |
|---|---|
| መጋዝ | መቅረጫ |
| አካፋ | መጽሐፍ |
| መዶሻ | ማስመሪያ |
| ሜትር | ቦርሳ |
| የብረት ማዕዘን | ደብተር |
| ዶማ | ላጲስ |
| ቆንጮራ | እርሳስ |
| መሮ | እስክርብቶ |
| መሰላል | ወረቀት |
| ማጭድ | |
| ዉሃ ልክ | |

## መልመጃ 7.2

1. ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በመመልከት የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች እና የቤት ቁሳቁስ በማለት መድቧቸዉ፡፡



2. ከዚህ በታች ያሉትን ምሥሎች በመመልከት የጓሮ አትክልት እና የእህል አይነቶች  በማለት በሰንጠረዥ አደራጁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
|  ድንች |  በቆሎ |  ነጭ ሽንኩርት |  ገብስ |
|  ቀይ ሥር |  አበባ ጎመን |  ቲማቲም |  ካሮት |
|  ጤፍ |  ቃሪያ |  ጥቅል ጎመን |  ቀይ ሽንኩርት |
|  ስንዴ |  ማሽላ |  ዱባ | |

## 7.3. ዕቃዎችን በመጠቀም መረጃ ማደራጀት እና መተንተን

መግቢያ፡

በዚህ ንዑስ ርዕስ የተሰበሰቡ ዕቃዎችን በሠንጠረዥ ለማደራጀት ጭረቶችን ተጠቅመን እንዴት በአሃዝ መጻፍ እንዳለብን ተጠቅሷል።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- በሠንጠረዥ የተደራጀዉን የመረጃ ዉጤት ትተነትናላችሁ።
- ዕቃዎችን በመጠቀም እንዴት መረጃዎች እንደምታደራጁ ትረዳላችሁ።

## ተግባር 7.3

1. የቤተሰቦቻችሁን አባላት ብዛት በመመዝገብ ወንድ እና ሴት በማለት ለይታችሁ አስቀምጡ፡፡
2. ከዚህ በታች የቀረቡ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ዘመናዊና እና ባህላዊ በማለት ብዛታቸዉን በጭረት እና በአሃዝ ግለጹ፡፡

   መኪና፣ ፈረስ፣ አዉቶቢስ፣ አህያ፣ ባጃጅ፣ ግመል፣ አዉሮፕላን፣ ብስክሌት፣ ሞተር ሣይክል

3. በክፍላችሁ ዉስጥ ያሉ ተማሪዎችን ብዛት በጾታ በጭረት እና በአሃዝ ሠንጠረዥ በመሥራት ግለጹ፡፡

### ማስታወሻ

*ዕቃዎችን በመጠቀም መረጃ ማደራጀት ማለት የተሠጡንን ወይም መረጃ የሰበሰብናቸዉን ዕቃዎች በየአይነታቸዉ ለይተን በጭረት እና በአሃዝ ሠንጠረዥ በመሥራት ብዛታቸዉን መጻፍ ነዉ፡፡ በጭረት ስንቆጥር ብዛታቸዉ ከአራት ሲበልጥ አምስተኛዉን ወደጎን በመሀላቸዉ እናሰምራለን፡፡*

ምሳሌ፡-

1. ከዚህ በታች ያሉ ዕቃዎችን የአርሶ አደር እና የአናጢ ዕቃ በማለት ብዛታቸዉን በጭረት እና በአሃዝ በሠንጠረዥ ግለጹ፡፡

   ሞፈር ፣ መጋዝ፣ ቀንበር፣ መዶሻ፣ ሞረድ፣ ማረሻ፣ ሜትር፣ ዶማ፣ ማጭድ፣ ዉሃ ልክ፣ ሲባጎ

መፍትሔ:

| | በጭረት | በአሃዝ |
|---|---|---|
| የአርሶ አደር ዕቃዎች | ~~\|\|\|\|~~ | 5 |
| የአናጺ ዕቃዎች | ~~\|\|\|\|~~ \| | 6 |

2. ከዚህ በታች ያሉ ምሥሎች በአይነታቸዉ በጭረት እና በአሃዝ ሠንጠረዥ በመሥራት ግለጹ፡፡



**መፍትሔ**

| | በጭረት | በአሃዝ |
|---|---|---|
| ሦስት ጎን | 𝍸 𝍸 \| | 11 |
| አራት ጎን | 𝍸 \|\|\| | 8 |
| ክብ | 𝍸 \|\| | 7 |

## መልመጃ 7.3

1. አስተማሪያችሁ የአምስት ተማሪዎችን ስማቸዉን ዕድሜያቸዉን እና ጾታቸዉን ከዚህ በታች ባለዉ ሠንጠረዥ መልክ ሰጥቷል፡፡ ሠንጠረዡን በማየት ቀጥለዉ ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

| የተማሪ ስም | ዕድሜ | ጾታ |
|---|---|---|
| አቡዱልቃድር ጀማል | 8 | ወንድ |
| ዮሐንስ ለማ | 10 | ወንድ |
| አበበ ዲታ | 12 | ወንድ |
| ፀሐይነሽ ጎቸራ | 8 | ሴት |
| ቡሉኬ ደንጎ | 15 | ሴት |

ሀ. ትንሽ ዕድሜ ያለዉ ተማሪ ማን ነዉ?

ለ. የወንድ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነዉ? የሴት ተማሪዎች ብዛት ስንት ነዉ?

ሐ. የወንዶችን እና የሴቶችን ብዛት በሠንጠረዥ ጭረት በመስራት በአሃዝ ገልጹ፡፡

2. ከዚህ በታች ያሉትን ዕቃዎች በገበያ እና በቢሮ የሚገኙ በማለት ብዛታቸዉን በጭረት እና በአሃዝ ሠንጠረዥ በመሥራት ግለጹ፡፡

ወንበር፣ ጨዉ፣ ሳሙና፣ ጠረጴዛ፣ ከረሜላ፣ ድንች፣ እስቴፕለር፣ ብስኩት፣ ስኳር፣ ኮምፒዩተር፣ ቡና፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ መደርደሪያ፣ ፎቶኮፒ

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ**

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በቅደሚያ መረጃዎችን እንዴት እንደሚሰበስቡ፣ የተሰበሰቡትን እንዴት እንደሚያደራጁ እና ያደራጁትን ወይም ተደራጅተዉ የተሰጡትን መረጃዎች በሠንጠረዥ እንዴት ብዛታቸዉን በጭረት እና በአሃዝ እንደሚገልጹ ተምረዋል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃዎች

1. የሚከተሉትን እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡
   ሀ. መረጃዎችን በመጠናቸዉ፣ በአይነታቸዉ እና በባህሪያቸዉ ለይቶ ማደራጃት ጠቃሚ ነዉ፡፡
   ለ. መረጃዎችን በጭረት እና በአሃዝ በሠንጠረዥ ማዘጋጀት ጊዜን ማባክን እንጂ ምንም ጥቅም የለዉም፡፡

2. የሚከተሉትን ሠንጠረዥ በመሥራት የቤት እንስሳት፤ ፍራፍሬዎች እና የትምህርት መሣሪያዎች በማለት አደራጁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብርቱካን | በቅሎ | ፍየል | ፈረስ |
| ቦርሳ | ማስመሪያ | ሎሚ | አናናስ |
| አህያ | አቦካዶ | ማንጎ | ሙዝ |
| ላም | ዉሻ | ድመት | ፓፓያ |
| ዶሮ | በሬ | እስክርብቶ | ደብተር |
| መጽሐፍ | እርሳስ | ላጲስ | በግ |

3. በትምህርት ቤታችሁ ያሉ የሁለተኛ ክፍል መምህራን ብዛት የሂሳብ መምህራችሁን ጠይቃችሁ ስማቸዉን በመጻፍ ወንድ

እና ሴት በማለት ብዛታቸዉን በጭረት እና በአሃዝ ሠንጠረዥ በመሥራት አሳዩ፡፡

# ምዕራፍ 8

## የጂኦሜትሪ ቅርጾች

**መግቢያ፡-**በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ ጎኖች እና ነቁጥ ያላቸዉ ባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች እነማን እንደሆኑ ተለይተዋል፡፡ በተጨማሪ ተመሳሳይ ምሥሎችን እንዴት በመጠናቸዉ ማወዳደር እንደሚቻል በዚህ ምዕራፍ ተጠቅሷል፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ባለሁለት አዉታር ቅርጾችን ትለያላችሁ፡፡
- ባለሁለት አዉታር ቅርጾችን በጎናቸዉ ብዛት እና በነቁጣቸዉ መሠረት ትሰይማላችሁ፡፡
- ጎኖች እና ነቁጦች የሌላቸዉን ባለሁለት አዉታር ቅርጾችን ትለያላችሁ፡፡
- ተመሳሳይ ምስሎችን በመጠናቸዉ ታወዳድራላችሁ፡፡

## 8.1 ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾችን በማየት መመደብ

**መግቢያ፡** በዚህ ንዑስ ርዕስ ባለ ሁለት አዉታር የሆኑ የጂኦሜትሪ ቅርጾች ከሌሎች እንዴት እንደሚለዩ ተገልጿል፡፡ስለዚህ ባለሁለት አዉታር ቅርጾችን ከሌሎች ለመለየት ይህንን ርዕስ በደንብ መማር ያስፈልጋል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ባለሁለት አዉታር ቅርጾችን ትለያላችሁ፡፡

ተግባር 8.1

1. ባለ ሁለት አዉታር ቅርጽ የሚባሉት ምን ዓይነት ምሥሎች ናቸዉ? ከቀጥታ መስመር ይለያሉ ወይስ አንድ አይነት ናቸዉ?
2. ባለ ሁለት አዉታር ቅርጽ የሆኑ ምሥሎችን በደብተራችሁ ሳሉ?

ማስታወሻ፡ ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾች የምንላቸዉ ስፋት ያላቸዉ ነገር ግን ዉፍረት የሌላቸዉ በጠፍጣፋ እና ዝርግ በሆነ ነገር ላይ ሙሉ በሙሉ መቀመጥ የሚችሉ ናቸዉ፡፡

**ምሳሌ ፡ሀ.** ከዚህ በታች ያሉ ባለ ሁለት አዉታር ምስሎች የተለያዩ ጎኖችና ነቁጦች አሏቸዉ



ለ. ጎን እና ነቁጥ የሌላቸዉ ነገር ግን ባለ ሁለት አዉታር ምስል የሆኑ



ሐ. ባለ ሁለት አዉታር ቅርጽ ያልሆኑ ምስሎች



## መልመጃ 8.1

1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሥሎች በመመልከት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡




ሀ. ባለ ሁለት አዉታር ምስሎች የትኞች ናቸዉ?

ለ. ባለ አንድ አዉታር ምስሎች የትኞች ናቸዉ?

ሐ. ባለ ሁለት አዉታር ሆነዉ ጎን የሌላቸዉን ጻፉ፡፡

መ. ከምስሎች አዉታር የሌለዉ የትኛዉ ነዉ?

2. ከዚህ በታች ያሉ ምስሎችን በመመልከት ቀጥሎ ያሉ ጥያቄዎችን ሥሩ፡፡




ሀ.ባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች የትኞች ናቸዉ?

ለ. ከላይ ካሉ ምሥሎች ዉስጥ የሂሳብ መጽሐፍ የሚመስሉት የትኞች ናቸዉ?

ሐ. ሦስት ጎን ያለዉ የትኛዉ ነዉ?

## 8.2 ቅርጾችን በጎናቸዉ እና በነቁጣቸዉ መግለጽ

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ባለሁለት አዉታር የሆኑ ምሥሎችን በጎናቸዉ እና በነቁጣቸዉ በመለየት ስያሜ እንዴት እንደሚሰጥ ተገልጿል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ባለሁለት አዉታር ምሥሎችን የጎናቸዉን እና የነቁጣቸዉን ስያሜ በመጠቀም ትገልጻላችሁ፡፡

**ተግባር 8.2**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባለሦስት ጎን ምሥሎች አሉ? እነማን ናቸዉ?
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባለ ሁለት አዉታር የሆኑ እና ጎን ያላችዉን ምስሎችን መዝግባችሁ በቡድን ተወያዩ፡፡

ማስታወሻ

- ሦስት ጎን ያላቸዉ ምሥሎች ባለሦስት ጎን ሲሆኑ ሦስት ነቁጥ አላቸዉ፡፡ አራት ጎን ያላቸዉ ምሥሎች ባለአራት ጎን ሲሆኑ አራት  ነቁጥ አላቸዉ፡፡ አራት ጎን ያላቸዉ ምሥሎች አራቱም አንግሎች ማዕዘናዉ ሆነዉ አራት ጎናቸዉ እኩል ከሆኑ ካሬ ይባላል፡፡ አራቱም አንግሎች ማዕዘናዊ ሆነዉ ሁለት ተቃራኒ ጎኖች እኩል ከሆኑ ሬክታንግል ይባላል፡፡ ጎን እና ነቁጥ ያላቸዉ ባለ ሁለት

አዉታር ምሥሎችን ስያሜ የምንሰጠዉ በነቁጣቸዉ ላይ ያሉ ሆሄያትን በመጠቀም ነዉ፡፡

ምሳሌ፡ የሚከተሉትን ምሥሎች በማየት ከሥዕሎች በታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡




ሀ. ባለ ሦስት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

ለ. ባለ አራት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

ሐ. ባለ አምስት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

መ. ባለ ስድስት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

መፍትሔ፡ሀ. ሦስት ጎን ሀለመ

ለ. አራት ጎን ሠረሸቀ እና አራት ጎን በተቸነ

ሐ. አምስት ጎን ኘአከኸወ

መ. ስድስት ጎን ዘዠየደጀገ

## መልመጃ 8.2

1. ከዚህ በታች ያሉ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመመልከት ቀጥሎ ያሉ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ሀ. ባለ ሦስት ጎን ምሥል የትኛዉ ነዉ?

ለ. ባለ አራት ጎን ምሥል የትኛዉ ነዉ?

ሐ. ከተሰጡት ምሥሎች አራት ጎኖች እኩል የሆኑ እና አራት አንግሎች እኩል የሆኑት የትኞች ናቸዉ?

መ. ከምሥሎች መካከል ባለ ሁለት አዉታር ያልሆኑ ምሥሎች አሉ? ካሉ የትኞች ናቸዉ?

2. ከዚህ በታች ላሉ ምሥሎች ስያሜ ስጡ፡፡




ሀ. ባለ ሦስት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

ለ. ባለ አራት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

ሐ. ባለ አምስት ጎን ምሥሎች እነማን ናቸዉ?

3. ከዚህ ቀጥሎ ላሉ ምሥሎች የጎናቸዉን እና የነቁጣቸዉን ብዛት በተሰጠዉ ቦታ ላይ ሙሉ።

| | ባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች | የጎኖችን ብዛት ጻፉ | የነቁጣቸዉን ብዛት ጻፉ |
|---|---|---|---|
| 1 |  | | |
| 2 |  | | |
| 3 |  | | |
| 4 |  | | |

## 8.3. ተመሳሳይ ምሥሎችን በመጠናቸዉ ማወዳደር

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተመሳሳይ ምሥሎችን እንዴት እንደሚናወዳድር፣ የትኞች ምሥሎች ከየትኞች ጋር እንደሚወዳደሩ ተገልጿል።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ተመሳሳይ ምሥሎችን በመጠናቸዉ ታወዳድራላችሁ፡፡

## ተግባር 8.3

1. ከዚህ በታች ከቀረቡት ምሥሎች ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸዉ ምሥሎች የትኞች ናቸዉ?



## ማስታወሻ

- ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸዉ ምሥሎች መጠናቸዉ ትልቅ ወይም ትንሽ ሊሆን ይችላል። ተመሳሳይ ጎን ያላቸዉ ምሥሎች የጎናቸዉ እና የነቁጣቸዉ ብዛት እኩል ነዉ።

ምሳሌ የሚከተሉትን ምሥሎች በመጠናቸዉ አወዳድሩ።




መፍትሔ፡ መጠናቸዉ አንድ አይነት የሆኑ ባለ ሦስት ጎን ምሥሎች ሀ እና ሠ፣ ባለ አራት ጎን ምሥሎች ለ፣መ እና ረ ናቸዉ።

የ ሀ መጠን ከ ሐ ያንሳል፣ የ ሠ መጠናቸዉ ከ ሐ ያንሳል።

የ መ መጠን ከ ለ ያንሳል።የ ረ መጠን ከ ለ መጠን ያንሳል።

## መልመጃ 8.3

1. ከዚህ በታች ያሉ ምሥሎችን በመመልከት ተመሳሳይ የሆኑትን ለይታችሁ በማዉጣት በመጠናቸዉ አወዳድሩ፡፡




2. የሚከተሉተን በመጠናቸዉ ከትንሽ ወደ ትልቅ በፊደላቸዉ አስቀምጡ፡፡



ሀ. ለ. ሐ.

## 8.4 ጠጣር ምስሎችን መለየት

**መግቢያ፡** ጠጣር ምስሎች ከባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች በምን እንደሚለዩ እና ያላቸዉን ቅርጽ ምን እንደሚመስል በዚህ ንዑስ ርዕስ ተገልጿል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ጠጣር ምሥሎችን ከሌሎች ምሥሎች ትለያላችሁ።

ተግባር 8.4

1. ጠጣር ምስል የምንላቸዉ ምን ይመስላሉ? ተወያዩ።
2. መጽሐፍ፣ ቦርሳ፣ ሰሌዳ፣ ሣጥን፣ ኳስ፣ ወረቀት፣ ቀጥታ መስመር፣ ነጥብ ከነኚህ ጠጣር ምሥሎች የምንላቸዉ የትኞች ናቸዉ?

ማስታወሻ፡ ጠጣር ምስሎች የምንላቸዉ ባለ አንድ እና ባለ ሁለት አዉታር ያልሆኑ ምሥሎች ስለሆኑ ጠፍጣፋና ዝርግ በሆኑ ነገሮች ላይ ተለጥፈዉ መቀመጥ የማይችሉ እና ዉፍረት ያላቸዉ ናቸዉ።

ምሳሌ፡ ከዚህ በታች ያሉ ጠጣር ምስሎች ናቸዉ፡፡



## መልመጃ 8.4

1. የምታዉቋቸዉን ጠጣር ምስሎች ስም ጻፉ፡፡
2. ከዚህ በታች ካሉ ምሥሎች ጠጣር ምሥሎችን የያዙ ፊደላትን ለይታችሁ ጻፉ፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጽ ያላቸዉ ምሥሎችን ማለትም ባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች መለየት፤ የጎናቸዉን እና የነቁጣቸዉን ብዛት መለየት ተምረዋል፡፡ በተጨማሪ ባለ ሁለት አዉታር ምሥሎች እንዴት እንደሚሰየሙ እና ጠጣር ምሥሎችን እንዴት ከባለ ሁለት አዉታር እንደሚለዩ ተገልጿል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ

   ሀ. ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾች ያላቸዉ የጎን መጠን ሦስት ወይም አራት ብቻ ነዉ?

   ለ. ነጥብ እና ቀጥታ መስመር ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾች አይደሉም፡፡

   ሐ. የሁለተኛ ክፍል የሒሳብ መማሪያ መጽሐፍ ባለ ሁለት አዉታር ቅርጽ ነዉ፡፡

   መ. ጎን እና ነቁጥ የሌላቸዉ ባለ ሁለት አዉታር ቅርጾች አሉ፡፡

2. በደብተራችሁ ባለ ሁለት አዉታር እና ባለ አንድ አዉታር ቅርጾችን ሳሉ፡፡

3. ከሚከተሉት ምሥሎች ተመሳሳይ ቅርጽ እና ተመሳሳይ መጠን ያላቸዉን እኩል ጎነ ሦስት፣ እኩል ጎነ አራት፣ እኩል ጎነ ስድስት እና እኩል ክብ በማለት ግለጹ።




4. ከሚከተሉት ጠጣር ምሥሎች የምታዉቋቸዉን ስማቸዉን ጻፉ።




## ምዕራፍ 9

# የኢትዮጵያ ገንዘብ

**መግቢያ፡** በዚህ ምዕራፍ የኢትዮጵያ የገንዘብ አይነቶችን እንዲሁም ገንዘቦች እንዴት እንደሚደመሩ እና እንደሚቀነሱ በምሳሌዎች ተገልጿል፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች በገንዘብ እንዴት መገበያየት እንዳለባችሁ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትረዳላችሁ፡፡

**የትምህርቱ ዓላማዎች፡**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የኢትዮጵያ የምንዛሬ አይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን ምንዛሬን በመጠቀም ገንዘብን ትደምራላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን ምንዛሬን በመጠቀም ገንዘብን ትቀንሳላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያን ገንዘብ በጨዋታ መልክ እንዴት መገበያየት እንዳለባችሁ ትገነዘባላችሁ፡፡
- ስለ ኢትዮጵያ ገንዘብ የተሰጡ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ፡፡

## 9.1. የኢትዮጵያን ምንዛሪ በመጠቀም ገንዘብን መደመር እና መቀነስ

**መግቢያ፡** የኢትዮጵያ የብር ኖቶች እና ሳንቲሞች በቅድሚያ ተገልጸዋል፡፡ በመቀጠል ኖቶችን እና ሳንቲሞችን በማጣጣም እንዴት መደመር እና መቀነስ እንዳለባችሁ በምሳሌዎች ተብራርቷል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የኢትዮጵያን የገንዘብ ኖቶችን ትለያላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን ምንዛሬ በመጠቀም ገንዘቦችን ትደምራላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን ምንዛሬ በመጠቀም ገንዘቦችን ትቀንሳላችሁ፡፡

## ተግባር 9.1

1. በኢትዮጵያ ምንዛሬ ዉስጥ ትልቁ የብር ኖት ማን ነዉ?
2. የኢትዮጵያ የሣንቲም ዲናሮችን ዘርዝሩ።
3. የኢትዮጵያን የብር ኖቶች ዘርዝሩ።
4. የኢትዮጵያ የመገበያያ ገንዘብ ምን ይባላል?

## ማስታወሻ

ገንዘብ ማለት ህዝቦች በመግባባት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎትን ለማግኘት የሚጠቀሙት የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ናቸዉ። የብሮች እና የሳንቲሞች አገልግሎት የዋጋ መጠን የተለያየ ሆኖ በመንግሥት የሚታተሙ ናቸዉ። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ የሚገኙ የብር ኖቶች ባለ ሁለት መቶ ብር፣ አንድ መቶ ብር፣ ሃምሳ ብር፣ አሥር ብር እና ባለ አምስት ብር ሲሆኑ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሳንቲም አይነቶች ባለ አንድ ብር ሣንቲም፣ ሃምሳ ሣንቲም፣ ሃያ አምስት ሣንቲም፣ አሥር ሣንቲም፣ አምስት ሣንቲም እና ባለ አንድ ሣንቲም ናቸዉ።

ምሳሌ፡ በኢትዮጵያ የሚገኙ የብር ኖቶች የሚከተሉት ናቸዉ።




ሁለት መቶ ብር




አንድ መቶ ብር




አምሳ ብር




አሥር ብር



አምስት ብር

በኢትዮጵያ የሚገኙ የሳንቲም ዲናሮች







የአንድ ብር ሳንቲም ሃምሳ ሳንቲም ሃያ አምስት







አሥር ሳንቲም አምስት ሳንቲም አንድ ሳንቲም

ምሳሌ፡

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. አንድ ባለ ሁለት መቶ ብር ኖት_____ባለ አምሳ ብር ኖቶች ይሆናሉ።

ለ. አንድ ባለ መቶ ብር ኖት_____ባለ አሥር ብር ኖቶች ይሆናሉ።

ሐ. አንድ ባለ ሃምሳ ብር ኖት_____ባለ አሥር ብር ኖቶች ይሆናሉ።

መ. አንድ ባለ አሥር ብር ኖት_____ባለ አምስት ብር ኖቶች ይሆናሉ።

መፍትሔ

ሀ. 4 ለ. 10 ሐ. 5 መ. 2

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ።

ሀ. 10 ብር + 50ብር ለ. 100 ብር + 200ብር

ሐ. 5 ብር + 13 ብር መ. 25 ሣንቲም + 10 ሣንቲም

ሠ. 100 ብር - 50 ብር ረ. 100 ሣንቲም-75 ሣንቲም

መፍትሔ

ሀ. 60 ብር ለ. 300 ብር ሐ. 18 ብር

መ. 35 ሣንቲም ሠ. 50 ብር ረ. 25 ሣንቲም

## መልመጃ 9.1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ደምሩ፡፡

ሀ. 2 ብር + 5 ብር = ___ ለ. 10 ብር + 6 ብር = ___

ሐ. 25 ብር + 3 ብር = ___ መ. 70 ሣ. + 32 ሣ. = ___

ሠ. 100 ሣ. + 50 ሣ. = ___ ረ. 50 ሣ. + 50 ሣ. = ___

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቀንሱ፡፡

ሀ. 25 ብር - 10 ብር = __ ለ. 30 ብር - 25 ብር = ___

ሐ. 89 ሣ. - 21 ሣ. = ___ መ. 95 ሣ. - 15 ሣ. =

___

## 9.2 በጨዋታ መልክ መገበያየት

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች በጨዋታ መልክ የተለያዩ ዕቃዎችን ወደ ክፍል በማምጣት ይገበያያሉ፡፡ ይህንን ለመተግበር የሚጠይቁ ጥያቄዎች በምሳሌዎች ተካትተዋል፤ የምንዛሪዎችን ዋጋ ማወቅም ጠቃሚ ነዉ፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የኢትዮጵያን ገንዘብ በመጠቀም በጨዋታ መልክ ትገበያያላችሁ፡፡

ተግባር 9.2

1. ሱቅ በመሄድ ምን ገዝታችሁ ታዉቃላችሁ?
2. የአንድ ዳቦ ዋጋ በአካባቢያችሁ ስንት ነዉ?
3. የኢትዮጵያ የብር ኖቶችን እና የሣንቲም ዲናሮችን በሙሉ ታዉቃላችሁ?

ማስታወሻ፡- በጨዋታ መልክ ተማሪዎች እንድገበያዩ የተለያዩ ዕቃዎችን ወደ ክፍል ማምጣት፡፡ ከዚህም የተለያዩ የገንዘብ ኖቶችን እና ሳንቲሞችን ለተማሪዎች በመስጠት እንዲገበያዩ ማድረግ፡፡

ምሳሌ

1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. የአንድ ደብተር ዋጋ 15 ብር ቢሆን የ ሦስት ደብተሮች ዋጋ ስንት ነዉ?

ለ. አበበ ሁለት ተመሳሳይ ብስኩት በ 20 ብር ቢገዛ የእያንዳንዱ ዋጋ ስንት ነዉ?

ሐ. የአንድ ሙዝ ዋጋ ስንት ነዉ?

**መፍትሔ**

1. ሀ. 45 ብር ይሆናል፡፡

   ለ. 10 ብር ነዉ፡፡

   ሐ. እንደየሙዝ መጠን ይለያያል፡፡

**መልመጃ 9.2**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

   ሀ. ሦስት ተማሪዎች ሻይ ጠጡ፡፡ የአንድ ሻይ ዋጋ አምስት ብር ቢሆን ተማሪዎች ስንት ብር ይከፍላሉ?

   ለ. አሥር ብር ስንት የአንድ ብር ሳንቲም ይሆናል?

   ሐ. አንድ እስክርብቶ 10 ብር ቢሆን 50 ብር ይዛችሁ ገበያ ብትሄዱ ስንት እስክርብቶ መግዛት ትችላላችሁ?

   መ. የአንድ ሙዝ ዋጋ 5 ብር ቢሆን 8 ተማሪዎች ገበያ ሄደዉ አንድ አንድ ተመጣጣኝ ሙዝ ቢገዙ ስንት ብር ይከፍላሉ?

## 9.3 የቃላት ፕሮብሌሞች

**መግቢያ:** በዚህ ርዕስ ተማሪዎች ስለኢትዮጵያ ገንዘብ የሚጠይቁ የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዴት እንደሚሰሩ በምሳሌዎች ስለተገለጸ ምሳሌዎችን መረዳት መልመጃዎችን በቀላሉ ለመስራት ያስችላል።

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት:-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-**

- የኢትዮጵያ ምንዛሬዎች እና መገበያየት ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ።

ተግባር 9.3

1. የአንድ ደብተር ዋጋ 32 ብር ቢሆን የ 3 ደብተሮች ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?

2. ሰብለወንጌል ልጇን ትምህርት ቤት ስታስገባ ለምዝገባ 40 ብር እና የአንድ ወር ክፍያ 350 ብር ብትከፍል በጠቅላላዉ ስንት ብር ከፍላለች?

ማስታወሻ፡ ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች የኢትዮጵያን ገንዘቦች በመጠቀም መገበያየት እንድችሉ የምንዛሪ አይነቶችን በሚገባ መረዳታቸዉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም ከገንዘብ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት እንድለማመዱ ማድረግ፡፡

ምሳሌ፡

1. የአንድ ሳሙና ዋጋ 20 ብር ቢሆን የአራት ሳሙና ስንት ብር ያወጣል፡፡

   መፍትሔ፡ 20 ብር+20 ብር+20 ብር+20 ብር = 80 ብር

2. የአንድ ቦርሳ ዋጋ 300 ብር ቢሆን ሁለት ቦርሳዎች በስንት ብር ይሸጣሉ?

   መፍትሔ 300 ብር + 300 ብር = 600 ብር

## መልመጃ 9.3

1. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ።

ሀ. ሩቅያ 500 ብር ይዛ ወደ ገበያ ሄደች። በ 150 ብር ዕንቁላል እና በ 250 ብር ዘይት ብትገዛ በጠቅላላ ስንት ብር አወጣች? ምን ያህል ብር ይቀራታል?

ለ. አቶ ካሌብ ዳቦ ቤት አለዉ። የአንድ ዳቦ ዋጋ 10 ብር ነዉ። አቶ ካሌብ በቀን 90 ዳቦዎችን ቢሸጥ በጠቅላላ ስንት ብር ያገኛል?

2. በአቶ ቤታ ሱቅ አንድ ኪሎ ስኳር 30 ብር፣ አንድ ሊትር ዘይት 27 ብር፣ አንድ ኪሎ ምሥር 80 ብር እና አንድ ኪሎ ሽምብራ 50 ብር ይሸጣል።

   ሀ. አበበች 2 ኪሎ ምሥር እና 3 ኪሎ ስኳር ቢትገዛ ለአቶ ቤታ ስንት ብር መክፈል አለባት?

   ለ. አቶ እንግዳ ከአቶ ቤታ ሱቅ 2 ሊትር ዘይት እና 4 ኪሎ ሽምብራ ለመግዛት ስንት ብር መክፈል አለበት?

### የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

ገንዘብ ማለት ህዝቦች በመግባባት ዕቃዎችን የሚገዙበት ወይም አገልግሎቶችን የሚያገኙበት የብር ኖቶች ወይም

ሳንቲሞች ናቸዉ። ተማሪዎች በጨዋታ መልክ በመገበያየት የኢትዮጵያ ገንዘቦችን ጥቅም እና እንዴት የንግድ ሥራ እንደሚከናወን መረዳት ይችላሉ።

**የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ።

ሀ. የኢትዮጵያ ብር ኖቶች የሚባሉት ባለ 200 ብር ፣ ባለ 100 ብር ፣ ባለ 50 ብር ፣ ባለ 10 እና ባለ 5 ብር ናቸዉ።

ለ. ባለ 200 ብር ኖት 2 ባለ 100 ብር ኖቶች ይሆናል።

2. የሚከተሉትን ደምሩ።

ሀ. 20 ብር + 25 ብር

ለ. 25 ብር+10 ብር

ሐ. 70 ብር+20 ብር

መ. 80 ብር+ 20 ብር

3. የሚከተሉትን ቀንሱ።

ሀ. 25 ብር - 5 ብር

ለ. 60 ብር - 40 ብር

ሐ. 50 ብር - 6 ብር

መ. 45 ሳንቲም - 25 ሳንቲም

ሠ. 50 ሳንቲም - 20 ሳንቲም

4. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞችን አስሉ፡፡

ሀ. ተማሪ አዳነች ሎሚ ለመግዛት 175 ሳንቲም እና ሙዝ ለመግዛት 225 ሣንቲም ብታወጣ በጠቅላላዉ ስንት ሳንቲሞችን አዉጥታለች?፣ ወደ ብር ስለወጥ ስንት ብር ይሆናል?

ለ. አቶ አማረ ከገበያ በ 1,000 ብር ሁለት ዶሮዎች ገዛ፡፡ አቶ አማረ ለዶሮዎች ባለ 200 የብር ኖት ቢከፍል ስንት የ 200 ብር ኖቶች ያስፈልጉታል?

ሐ. አቶ ተሰማ 600 ብር ይዞ ገበያ በመሄድ በ 270 ብር ሱሪ እና በ 100 ብር ሸምዝ ገዛ፡፡ በጠቅላላዉ ስንት ብር ወጪ አወጣ? ስንት ብር ይቀረዋል?

# ምዕራፍ 10

## የኢትዮጵያ ጊዜ

**መግቢያ፡-** በዚህ ምዕራፍ ጊዜን እንዴት መለካት እንደሚቻል እና ጊዜ ለመለካት ምን አይነት መሣሪያዎችን መጠቀም እንዳለብን ተብራርቷል፡፡

### የትምህርቱ ዓላማዎች

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የዲጂታል እና የአናሎግ ሰዓት ዓይነቶችን በመጠቀም ጊዜን በሰዓት፣ በግማሽ ሰዓት እና በሩብ ሰዓት ትናገራላችሁ፡፡
- በሰዓት እና በደቂቃ መካከል ያለዉን ዝምድና ትገነዘባላችሁ፡፡
- ጊዜን የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ፡፡

## 10.1 በድጅታል እና በአናሎግ ሰዓት ጊዜን በአንድ ሰዓት፣ በግማሽ ሰዓት እና በሩብ ሰዓት መቁጠር

**መግቢያ፡-** በኢትዮጵያና በሌሎች አገራት ጊዜን በተለያዩ መንገዶች የተለያዩ የጊዜ መለኪያዎችን በመጠቀም ይለካሉ፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ጊዜን ለመለካት የተጠቀምነዉ ዘመናዊ የጊዜ መለኪያ ምድቦች ሰዓት፣ ደቂቃ እና ሴኮንድ ሲሆኑ ይህንንም በሁለት የሰዓት አይነቶች ማለትም በድጅታል ሰዓት እና በአናሎግ ሰዓት እናያለን፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የድጅታል እና የአናሎግ ሰዓት አይነቶችን ይለያሉ፡፡
- አንድ ሰዓት፣ ግማሽ ሰዓት እና ሩብ ሰዓት ልዩነታቸዉን ትገነዘባላችሁ፡፡

## ተግባር 10.1

1. ጧት ከእንቅልፋችሁ የምትነሱት በስንት ሰዓት ነዉ?
2. ጧት ትምህርት የምትጀምሩት በስንት ሰዓት ነዉ?
3. የጊዜ መለኪያ ምንድ ነዉ?
4. እቤታችሁ ወይም በሌላ ቦታ ምን አይነት ሰዓት አይታችሁ ታዉቃላችሁ? የምታዉቁትን የሰዓት አይነት ተነጋገሩ።
5. አንድ ሰዓት፣ ግማሽ ሰዓት እና ሩብ ሰዓት ስንል ምን ማለታችን ነዉ?

## ማስታወሻ

- ሰዓት የጊዜ መለኪያ ነዉ። ጊዜ በሰዓት፣ በደቂቃ እና በሴኮንድ ምድቦች ይለካል።
- ጊዜን ለመለካት የተለያዩ የሰዓት አይነቶችን መጠቀም እንችላለን። የተለያዩ የሰዓት አይነቶች በሁለት ይመደባሉ። እነርሱም ዲጅታል ሰዓት እና አናሎግ ሰዓት ናቸዉ።



ድጂታል ሰዓት



አናሎግ ሰዓት

ምሳሌ 1. የሚከተሉትን ሰዓቶችን ድጅታል ሰዓት ወይም አናሎግ ሰዓት በማለት ለዩ፡፡

ሀ. 

ለ. 
ሐ· 


ሰ.

መ 
ሠ. 
ረ· 

**መፍትሔ፡-** ሀ ፣ ሐ ፣ ሸ እና ቀ ዲጂታል ናቸዉ

ለ ፣መ፣ ሠ ፣ ረ እና ሰ አናሎግ ናቸዉ፡፡

**ምሳሌ፡ 2**

የእጅ ሰዓት፣ የግድግዳ ሰዓት፣ የጠረጴዛ ሰዓት ወዘተ አናሎግ ናቸዉ ወይስ ድጅታል ናቸዉ?

**መፍትሔ፡** ድጅታልም እና አናሎግም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡




ማስታወሻ፡-

የአናሎግ ሰዓት የተለያዩ ክፍሎች ስያሜ በዚህ ስዕል ላይ ይገኛል፡፡

ሰዓትን አንድ ሰዓት የምንለዉ ሙሉ ሰዓት ሲሆን ነዉ፡፡ ይህም በዲጂታል በቁጥር ሲገለጽ 1 ሰዓት (1፡00)፤ 2 ሰዓት (2፡00) --- በመባል ይገለጻል፡፡ በአናሎግ አንድ ሰዓት የሚንለዉ  የሰዓት ቆጣሪ  1 ሰዓት ሲያመለክት እና የደቂቃ ቆጣሪ 12 ላይ ሲያመለክት  1 ሙሉ ሰዓት እንላለን፡፡ በአናሎግ የደቂቃ ቆጣሪ 6 ላይ ሲያመለክት ከግማሽ ሰዓት  እንድሁም የደቂቃ ቆጣሪ 3 ላይ ሲያመለክት ከሩብ እንላለን፡፡

ምሳሌ 1. ሙሉ ሰዓት የምንላቸዉ

በዲጂታል  2፡00 ፤  3፡00፤    4፡00፤   8፡00፤ 12፡00

በአናሎግ




ምሳሌ 2. ከግማሽ ሰዓት የምንላቸዉ

በዲጂታል 2:30 ፣ 7:30 ፣ 11:30 ፣ 6:30



በአናሎግ አንድ ሰዓት ከግማሽ ስምንት ሰዓት ከግማሽ አራት ሰዓት ከግማሽ

ምሳሌ 3. ከሩብ ሰዓት የምንላቸዉ

በዲጂታል 3:15 5:15 9:15 11:15

በአናሎግ



አንድ ከሩብ (1:15) ስምንት ከሩብ (8:15) አራት ከሩብ (4:15)

**መልመጃ 10.1** የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. የሚከተሉትን የዲጂታል ሰዓቶች ሙሉ ሰዓት፣ ግማሽ ሰዓት እና ሩብ ሰዓት በማለት ለይታችሁ ጻፉ።

   ሀ. 2:15 ለ. 5:30 ሐ. 6:00 መ.8:30

   ሠ.10:15 ረ.12:00

2. የሚከተሉትን የአናሎግ ሰዓቶች ሙሉ ሰዓት፣ ግማሽ ሰዓት እና ሩብ ሰዓት በማለት ለይታችሁ ጻፉ።



ሀ ለ ሐ መ

3. የሚከተሉትን የአናሎግ ሰዓቶች በማንበብ ስንት ሰዓት እንደሆኑ በተሰጠዉ ቦታ ላይ ጻፉ።

ሀ.  ____________

ለ.  ____________

ሐ.  ____________

መ.  ____________

4. የሚከተሉትን ሰዓቶች ወደ አናሎግ በመቀየር በሥዕል አሳዩ።

ሀ. 2:30 ለ. 3:15 ሐ. 7:00 መ. 9:30

## 10.2. ሰዓት እና ደቂቃ

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ በሰዓት እና በደቂቃ መካከል ያለዉን ልዩነት እና ከሰዓት ወደ ደቂቃ እንዴት እንደሚቀየር እንድሁም ደቂቃ ምን እንደሆነ ቀርቧል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ደቂቃ በአናሎግ ሰዓት እንዴት እንደሚቆጠር ትለያላችሁ፡፡
- ሰዓትን ወደ ደቂቃ እንዴት እንደሚቀየር ትረዳላችሁ፡፡

ተግባር 10.2

1. 60 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነዉ?
2. 30 ደቂቃ ስንት ሰዓት ነዉ?
3. አንድ ሰዓት ስንት ደቂቃዎች አሉት?
4. ሁለት ሰዓት ስንት ደቂቃ ነዉ?

ማስታወሻ፡- በአናሎግ ሰዓት በእያንዳንዱ ቁጥር መካከል ያሉ ክፍት ቦታዎች ሲሆኑ ይህም የደቂቃ ቆጣሪ ከአንዱ ቁጥር እስከሚቀጥለዉ ቁጥር ሲደርስ 5 ደቂቃ ይሆናል፡፡ በዚህ ዓይነት የደቂቃ ቆጣሪ አንድ ሙሉ ዙር ሲዞር 60 ደቂቃ ይጓዛል፡፡ ይህም አንድ ሰዓት ይሆናል፡፡

ስለዚህ 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ

ግማሽ ሰዓት = 30 ደቂቃ ነዉ፡፡

ሩብ ሰዓት = 15 ደቂቃ ነዉ፡፡

ምሳሌ 1 የሚከተሉት የአናሎግ ሰዓቶች ስንት ሰዓት እንደሚያመለክቱ ጻፉ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ . 

መ. 

**መፍትሔ:** ሀ. 8፡05 ለ. 2፡20

ሐ. 10፡40 መ. 5፡35

**መልመጃ 10. 2**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. ስልሳ ደቂቃ ስንት ሰዓት ነዉ?

ለ. በአንድ ቀን ስንት ሰዓት አለ?

ሐ. በግማሽ ቀን ስንት ሰዓት አለ?

መ. 24 ሰዓት ስንት ቀን ነዉ?

2. የሚከተሉትን ሰዓቶች በመመልከት ስንት ሰዓት እንደሆኑ ጻፉ።

ሀ. 

______________

ለ. 

______________

ሐ. 

______________

መ. 

______________

3. የሚከተሉትን ሰዓቶች የአናሎግ ሰዓት በመሳል አመልክቱ፡፡

ሀ. 2፡45 ለ. 5፡00 ሐ. 9፡25 መ. 11፡55

## 10.3. የቃላት ፕሮብሌሞች

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ የሰዓት እና የደቂቃ ጥያቄዎች የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች በተግባር ጥያቄ እና በምሳሌ የቀረቡ ስለሆነ አሠራራቸዉን በመረዳት መልመጃዎችን መሥራት ይቻላል፡፡

**የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡-**

**ከዚህ ንዑስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ስለ ሰዓት እና ደቂቃ የሚጠይቁ የተለያዩ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትሰራላችሁ፡፡

## ተግባር 10.3

1. በትምህርት ቤታችሁ የዕረፍት ሰዓት ምን ያህል ነዉ?
2. ሰራዊት ከቤትዋ ጧት 1፡30 ተነስታ በ 2፡00 ሰዓት ወደ ትምህርት ቤት ደረሰች። ሰራዊት የተጓዘችዉ ስንት ደቂቃ ነዉ?
3. የሂሳብ አስተማሪ በ 3፡00 ሰዓት ወደ ክፍል ገብቶ በ 4፡00 ሰዓት ላይ ቢወጣ በጠቅላላዉ ምን ያህል ሰዓት አስተማረ?

## ማስታወሻ

- አንድን ቀን በብዙ ቦታ ከፋፍለን መግለጽ እንችላለን። ከነዚህም ጠዋት፣ እኩለ ቀን፣ ማታ ወይም ሌሊት እና እኩለ ሌሊት ዋና ዋናዎች ናቸዉ። አንድ ቀን ስንል ቀንና ማታዉን አንድ ላይ ነዉ። ስለዚህ አንድ ቀን 24 ሰዓት ይሆናል።
- በአናሎግ ሰዓት ላይ የሚገኙ አመላካች ቀስቶች
    - አጭር እና ወፍራም የሰዓት ቆጣሪ
    - ቀጭን እና ረዥም የሴኮንድ ቆጣሪ
    - በቁመቱ መካከለኛ እና ዉፍረቱም መካከለኛዉ የደቂቃ ቆጣሪ
    - 

ምሳሌ

1. አበበ ከትምህርት ቤት እስከ ቤቱ ደርሶ መልስ አንድ ሰዓት ተኩል ቢፈጅበት በደቂቃ ምን ያህል ይሆናል?

መፍትሔ፡ 90 ደቂቃ ይሆናል፡፡

2. ለማ 30 ደቂቃ ስፖርት ሊሰራ ሰዉነቱን አሟሟቀ፡፡ ቀጥሎ ለአንድ ሰዓት ተኩል ኳስ ተጫወተ፡፡ ሰዉነቱን ለማሟሟቅ እና ኳስ ለመጫወት ምን ያህል ጊዜ ፈጀበት?

መፍትሔ፡ 120 ደቂቃ ወይም 2 ሰዓት ፈጀበት፡፡

**መልመጃ 10.3**

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ሥሩ፡፡

1. አበራሽ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ከትምህርት ቤት ወደ ቤታቸዉ ስትሄድ 30 ደቂቃ ይፈጅባታል፡፡ አበራሽ ከትምህርት ቤት ወደቤታቸዉ ደርሶ መልስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድባታል?
2. አቶ ተክሉ ከአርባምንጭ ወደ ሀዋሳ በመኪና 4 ሰዓት ፣ ከሀዋሳ ወደ አዲስ አበባ ደግሞ 4 ሰዓት ቢወስድበት በጠቅላላ ከአርባምንጭ እስከ አዲስ አበባ ምን ያህል ሰዓት ወሰደበት?

3. ቀነኒሳ እና ስለሺ 1,000 ሜትር ሲሮጡ ቀነኒሳ ሩጫዉን በ 24 ደቂቃ ስጨርስ ስለሺ ደግሞ በ 27 ደቂቃ ጨረሰ። ቀድሞ የገባዉ ማን ነዉ? በስንት ደቂቃ ቀደመ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ማስታወሻ

ጊዜን ለመለካት የተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ መለኪያዎች ያሉ ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ጊዜን ለመለካት የተጠቀምነዉ ዘመናዊ መለኪያ ሰዓት እና ደቂቃን ነዉ። ጊዜን ለመለካት የምንጠቀመዉ መለኪያ መሣሪያ ሰዓት ሲሆን ሁለት የሰዓት አይነቶች ማለትም ድጂታል እና አናሎግ የሰዓት አይነቶች አሉ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ

ሀ. አንድ ቀን ሃያ አራት ሰዓት ነዉ።

ለ. አንድ ሰዓት ስልሳ ደቂቃ ነዉ።

ሐ. አንድ ሰዓት ተኩል በዲጂታል ሰዓት ሲጻፍ 1፡45 ነዉ።

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በዲጂታል ሰዓት ጻፉ።

ሀ. ሁለት ሰዓት ከ አርባ አምስት ደቂቃ

ለ. አንድ ሰዓት ከ ሃያ አምስት ደቂቃ

ሐ. ስድስት ሰዓት ከ ሃምሳ ደቂቃ

መ. ሶስት ሰዓት ከ አስራ አምስት ደቂቃ

3.የሚከተሉትን ጥያቄዎች የአናሎግ ሰዓት በመሳል አመልክቱ

ሀ. 3 ሰዓት ከ30 ደቂቃ    ለ. 7 ሰዓት ከ 30 ደቂቃ

ሐ. 6 ሰዓት    መ. 12 ሰዓት

4.የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞችን ሥሩ፡፡

ሀ. በእግር ኳስ ጨዋታ የመጀመሪያ ዙር የሚካሄደዉ 45 ደቂቃ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ዙር በተመሳሳይ 45 ደቂቃ ይካሄዳል፡፡ በጠቅላላዉ ጨዋታዉ ምን ያህል ሰዓት ይካሄዳል?

ለ. አቶ ገዛኸኝ የማራቶን ሯጭ ነዉ፡፡ በቶክዮ በተካሄደዉ የማራቶን ሩጫ 2 ሰዓት ከ 50 ደቂቃ ሩጫዉን አጠናቀቀ፡፡ ከወር በኋላ በለንደን በተካሄደዉ ሩጫ የማራቶኑን ሩጫ ለመጨረስ 2 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ ፈጀበት፡፡ አቶ ገዛኸኝ በሁለቱ ከተሞች በድምሩ ምን ያህል ሰዓት ነዉ የሮጠዉ?

በሰዓቶች መካከል ያለዉ ልዩነት ምን ያህል ነዉ?

# ሒሳብ

# የተማሪዉ መጽሐፍ

# ሁለተኛ ክፍል

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ